# መንፈስ ቅዱስ

ከዳንኤል መኰንን

ታኅሣሥ ፲፱፻፹፩ ዓ. ም.

# THE HOLY SPIRIT

by
Daniel Makonnen

*Second Printing*
*1987 Kingdom Life Publishing*

For Additional Copies Write:
Kingdom Life Publications
P.O. Box 78689
Seattle, WA 98178

Printed in U.S.A.

ይህን መጽሐፍ ምንም ጊዜ በአገልግሎቴ እየደገፉ ለሚያበረታቱኝ ወላጆቼ ከልባዊ ፍቅር ጋር ለማስታወሻ እንዲሆን አቀርባለሁ ።

ዳንኤል መኰንን ።

## ማ ው ጫ ።

ገጽ ።

መግቢያ - - - - - - - - - - - - - - - - - 5

ክፍል አንድ

መንፈስ ቅዱስ ማን ነው? - - - - - - - - - - - - - 7

መንፈስ ቅዱስና ሥላሴ - - - - - - - - - - - - - 13

መንፈስ ቅዱስ የተጠራበት ስሞችና ምሳሌዎች - - - - - - 17

መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን - - - - - - - - - - 22

መንፈስ ቅዱስና አዲስ ልደት - - - - - - - - - - 27

ኢየሱስና መንፈስ ቅዱስ - - - - - - - - - - - - - 30

ክፍል ሁለት

የመንፈስ ቅዱስ ዘመን - - - - - - - - - - - - - 35

በልሳን መናገር - - - - - - - - - - - - - - 42

ምስክርነት ፤ የብርሃን ኳስ ይመስል ነበር ፤

በደስታ ጐርፍ ተጥለቀለቁ ፤

እንደ ኤሌክትሪክ ኃይል ፤

የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ለምን ይጠቅማል? - - - - - - - 53

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች - - - - - - - - - - - - - 58

የመንጸት ስጦታዎች - - - - - - - - - - - - - - - 60

መተርጐም ፤

ትንቢት ፤

የመገለጥ ስጦታዎች - - - - - - - - - - - - - - - 73

ዕውቀት መናገር ፤

ጥበብ መናገር ፤

መናፍስት መለየት ፤

የኃይል ስጦታዎች - - - - - - - - - - - - - - - 79

ታምራት ፤

ፈውስ ፤

እምነት ፤

ማጠቃለያ ፤ - - - - - - - - - - - - - - - - - 83


# መ ግ ቢ ያ ።

ዛሬ መንፈስ ቅዱስ በአብያተ ክርስቲያናት ዘንድ የምዕመንና የአገልጋዮችን ስሜት የሳበ አርዕስት ሆኖአል ። ይህም የመንፈስ ሥራ ሲሆን ያለንበትም ዘመን የመንፈስ ቅዱስ ዘመን በመሆኑ ነው ። በመጽሐፉ ውስጥ ያለው ሃሳብ የተወሰኑ አብያተ ክርስቲያናትን ወይም ሰዎችን የማይመለከት በመሆኑ ክርስቲያኖች ሁሉ ሊያነቡት ይገባል ።

በአብያተ ክርስቲያናት አካባቢ የሚታየው አስገራሚ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እያደገ በመሄድ ላይ ነው ። ስለ መንፈስ ቅዱስ ስንናገር በእኛ ሕይወት የተፈጸመውን ወይም በሰዎች ሕይወት የሆነውን በመናገር መደምደም የለብንም ፣ አንድን ሰው ለማወቅ ስለጠባዩ ፣ ስለ ሥራው መረዳት እንደሚኖርብን እንዲሁም ስለ መንፈስ ቅዱስ ዶክትሪን ፣ ሥራና ጠባይ ማወቅ ይኖርብናል ። በሌላ አቅጣጫ ስለ ስጦታዎች የምንሰማውና የምንመለከተው ብዙ ሲሆን ስለ አጠቃቀማቸውና አሠራራቸው የምናውቀው ጥቂት ነው ።

ስለዚህ ይህ መጽሐፍ በሁለት ክፍል ተከፍሏል ። የመጀመሪያው ክፍል ስለ መንፈስ ቅዱስ መሠረታዊ ዶክትሪን የሚያስረዳ ሲሆን ሁለተኛው ክፍል የመንፈስ ቅዱስ ዘመን የሚል ሆኖ ከመንፈስ ቅዱስ ሙላት እስከ ስጦታዎች ያለውን የሚገልጽ ነው ። መጽሐፉ ይህን የመሰለ መልክ ያለው ሆኖ የትኛውንም ቤተ ክርስቲያን የማይነቅፍ ሚዛናዊ በሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ላይ የተመሠረተ ነው ።

በሁለተኛው ክፍል የመንፈስ ቅዱስ ዘመን በሚለው ውስጥ ባሉት ምዕራፎች የአንዳንድ ሰዎች ምስክርነት አቅርቤአለሁ ። ይህም አንባቢዎች ትምህርት የሆነውን ነገር ብቻ በማንበብ ሃሳቡ እንዳይከብዳቸውና ሃሳቡን እንዲጨብጡት ለማድረግ ነው ። ስጦታዎችን በሚመለከቱት ገጾች አልፎ አልፎ የራሴን ልምምድ እንደ ምሳሌ አድርጌ አቅርቤአለሁ ። ይህም ስጦታዎችን በመለማመድ ጀማሪ ለሆኑት ትምህርት ይሰጣቸዋል በማለት ነው ።

በመጨረሻ ለአንባቢዎቼ ለመግለጽ የምፈልገው ይህ መጽሐፍ ለአንባቢዎች እንዲደርስ ሃሳብ በመስጠት ፣ በማረም ፣ ታይፕ በማድረግ ለረዱኝ ከፍ ያለ ምሥጋና አቀርባለሁ ። ከሁሉ በላይ ግን አስጀምሮ ላስጨረሰኝ አምላክ ምስጋና ይድረሰው ።

ዳንኤል መኰንን ።

## ክፍል አንድ

### ምዕራፍ ፩ ፤

# መንፈስ ቅዱስ ማን ነው?

መንፈስ ቅዱስ ሰፊ እርእስት በመሆኑ መንፈስ ቅዱስ ማን ነው? የሚለው ጥያቄ ለመጽሐፉ ትክክለኛ ቁልፍ ይሆናል ብዬ አምናለሁ ። በየትኛውም ክፍለ ዘመን ቢሆን የአንድ መንፈስ ኀልውና በመረዳት ስለ መንፈስ ወይም ስለ መናፍስት ለማወቅ የሰው ልጅ የተቻለውን አድርጐአል ። ዛሬም በጌታ በኢየሱስ አምነን የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ያገኘን ሁሉ ስለ እርሱ ለማወቅ እጅግ እንናፍቃለን ። እርሱም የጥበብና የመገለጥ መንፈስ ነው ። ስለዚህም ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች ሲጽፍ «የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ» ይላል ። ይህ የሐዋርያው ብቻ ሳይሆን የእያንዳንዳችን ጸሎት ነው ።

«ሩሀ» የሚለው የዕብራይስጥ ቃል ወይም «ኑሚያ» የሚለው የግሪክ ቃል መንፈስ ማለት ነፋስ ወይም ትንፋሽ እንደሆነ ያስረዳናል ። መጽሐፍ ቅዱስ «እግዚአብሔር መንፈስ ነው» ይላል መላእክት ቅዱሳንና እርኩሳን «መናፍስት» ተብለው ይጠራሉ ። የሥላሴ ሦስተኛ አካል መንፈስ ተብሎ ይጠራል ። «ቅዱስ» የሚለው ቃል ባሕርይውን ስለሚገልጽ «መንፈስ ቅዱስ» ይባላል ። በተቀረ በተለይ በብሉይ ኪዳን አንዳንዴም በአዲስ «መንፈስ» በመባል ይጠራል ። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ኃይል በመሆኑና እግዚአብሔር ሥራውን በሦስተኛው አካል ስለሚፈጽም ነው ፤ ስለዚህም የእግዚአብሔር ኃይል በመሆኑ በሐዋርያት ሥራ ፩ ፣ ፰ ፣ «መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ» የሚል እናነባለን ። ነገር ግን የመንፈስ ቅዱስን ማንነት በዚህ ጥቅስ ላይ ብቻ በመመሥረት መንፈስ ቅዱስ አካል የሌለው የእግዚአብሔር ኃይል ብቻ ነው ማለት ትልቅ ስህተት ነው ።

#### ሀ/ መንፈስ ቅዱስ አካል አለው ፤

«መንፈስ ቅዱስ እንደ ሰው አካል ያለው አምላክ ነው» የሚለው የቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ ትምህርት አንዳንድ ሰዎች የማይቀበሉት አነጋገር ነው ። ይህ ችግር ዛሬ ብቻ ሳይሆን የጥንቲቷን ቤተ ክርስቲያን የገጠማት ነው ። በየጊዜው የተነሱ መናፍቃን የመጀመሪያ ተቃውሞአቸው በኢየሱስ አምላክነትና በመንፈስ

ቅዱስ ላይ ነው ። ወደ ኋላ ተመልሰን የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ ብንመለከት ዛሬ ድምጻቸውን በተቃውሞ የሚያሰሙ መሠረታቸው አልፎ አልፎ በየዘመኑ ከተነሱት መናፍቃን የሚለይ አይደለም ።

በሦስተኛው ክፍለ ዘመን ሳቢሊየስ የተባለ በሰሜን አፍሪቃ በሚገኝ የአንድ ቤተ ክርስቲያን መሪ የሥላሴን ትምህርትና መንፈስ ቅዱስ አካል የለውም በማለት ተቃውሞ ተከታዮችን አገኘ ፣ ከዚያም አርዮስ በኋላም መቅዶንዮስ ተቃውሟቸውን በመቀጠል እስከዚህ ዘመን ድረስ ሃሳባቸውን የሚደግፉ ሰዎች ፣ አሉ ፤ በዚህም ምክንያት የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን እስከዚህ ዘመን ድረስ ትምህርቱንና ሀሳቡን በመቃወም ላይ ትገኛለች ። ስለዚህ «መንፈስ ቅዱስ እንደ ሰው አካል ያለው አምላክ ነው» የሚለው ትምህርት የዛሬይቱም እውነተኛ ቤተ ክርስቲያን የምትከተለው ትምህርት ነው ።

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል ስለ መንፈስ ቅዱስ ምን ይላል ማለቱ የበለጠ ጠቃሚና ለጥያቄያችን መልስ ነው ። ስለዚህ ወደ እግዚአብሔር ቃል ተመልሰን መመልከት ይኖርብናል ፤ ነገር ግን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ገብተን ከመመልከታችን በፊት፤ «መንፈስ» «የእግዚአብሔር መንፈስ» «መንፈስ ቅዱስ» የሚለው ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ በብዙ ሥፍራ ተጠቅሶ እናያለን ። በአዲስ ኪዳን ብቻ ከሦስት መቶ ጊዜ ያላነሰ ተጠቅሶአል ። በተጠቀሰበት ሥፍራ አንዳንዴ እንደ ኃይል አንዳንዴም አካል እንዳለው ሰው ተገልጦ እናያለን ፤ ቢሆንም የምንሰጠው ትርጉም አንድ መሆንና እንደ ሰው ወይ እንደ ኃይል ብቻ ልንተረጉመው ይገባል ። ስለዚህ የራሳችንን ትርጉም ወደጐን አድርገን የእግዚአብሔርን ቃል እንዲተረጉም ካደረግን ችግር አይገጥመንም ። በሉቃስ ፫ ፣ ፳፪ «በአካል መልክ እንደ ርግብ በእርሱ ላይ ወረደ» የሚል እናያለን ። ከዚህ ጥቅስ መንፈስ ቅዱስ እንደ ሰው አካል እንዳለው ስንመለከት በዚህ ወንጌል መጨረሻ «ከላይ ኃይል እስክትቀበሉ ከኢየሩሳሌም አትውጡ» የሚለው የእግዚአብሔር ኃይል እንደሆነ ያስረዳናል ። ስለዚህ ነው ከላይ አንዳንዴ አካል እንዳለው ሰው አንዳንዴም እንደ ኃይል ቢጠቀስ የምንሰጠው ትርጉም አንድ ሊሆን ይገባል ያልኩት ። ታዲያ መንፈስ ቅዱስ አካል ያለው አምላክ ነው ወይስ ኃይል ብቻ ነው? እጭሩ መልስ መንፈስ ቅዱስ አካል ያለው (አምላክ) የእግዚአብሔር ኃይል ነው ።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች ፤

ከሁሉ በፊት መጽሐፍ ቅዱስ ለሰው የሚሰጠውን ሰዋስዋዊ አነጋገር ለመንፈስ ቅዱስ ሰጥቶት እናያለን ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከየትም ሥፍራ ይልቅ ስለ መንፈስ ቅዱስ የተናገረባቸው ምዕራፎች ዮሐንስ ፲፬ ፣ ፲፮ ናቸው ። በእነዚህ ምዕራፎች ጌታ መንፈስ ቅዱስን «እርሱ» በማለት ይጠራዋል ። ስለራሱ ሲናገር «እኔ» በሌላ ሲጠራ «እርሱ» የሚባል አካል ያለው ሰው ነው ። ስለዚህም ኢየሱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ በሚናገርበት ጊዜ እርሱ የሚለውን የተውላጠ ስም ቃል ተጠቀመ ። «ለዘላለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል ። እርሱም ዓለም



የማያየውና የማያውቀው ስለሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው።» ዮሐ. ፲፬ ፣ ፲፮—፲፯ «አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል» ፲፬ ፣ ፳፮ ጌታ ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስን እርሱ በማለት ከመጥራቱም ሌላ «ወደ እርሱ እንመጣለን ። በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን» ሲል ተናገረ ፣ ይህ አነጋገር አብን ብቻ ሳይሆን መንፈስ ቅዱስንም እንደሚያጠቃልል ከመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ማስረጃዎች አሉ ። ሌላው ደግሞ ሊጠቀስ የሚገባው ቃል «አጽናኝ» የሚለው ነው።«አጽናኝ» ማለት በግሪክ «ጳራቅሊጦስ» ሲሆን የሚሰጠው ትርጉም አጽናኝ ከሚለው በላይ ነው ፤ ስለዚህ «አማካሪ» «ጠበቃ» ተብሎ ይተረጐማል ። ከዚህ ትርጉም አያይዘን የጥንቱ የግሪክ ፍርድ ቤት ለጠበቃ ወይም ስለሌላው ሰው ለሚናገረው የሚሰጠው ስም ጳራቅሊጦስ የሚል ነበር ። ከዚህም አጠቃቀሙ ለሰው እንጂ ለነፋስ ወይም አካል ለሌለው ነገር እንዳልሆነ እንመለከታለን ።

መንፈስ ቅዱስ እንደ ሰው አካል ያለው ነው ካልን የሰው ባሕርያት ልናይበት ይገባል ። ስለዚህ እንደ ሰው ፈቃድ አለው ። ፩ ቆሮ. ፲፪ ፣ ፲፩ ፤ ሃሳብ አለው ሮሜ. ፰ ፣ ፳፯ ፤ ዕውቀት አለው ፩ ቆሮ. ፪ ፣ ፲ ፣ ፲፩ ፤ ይህ ብቻ ሳይሆን ከዚህ በታች ያሉት ጥቅሶች አካል እንዳለው ያረጋግጣሉ ።

## እንደ ሰው ይሠራል ፤

| | |
|---|---|
| በአማኞች ይኖራል | ዮሐ ፲፬ ፣ ፲፯ |
| ያስተምራል ፣ | » ፲፬ ፣ ፳፮ |
| ስለ ኃጢአት ይወቅሳል | » ፲፮ ፣ ፰ |
| ይመራል ፣ ይሰማል ፣ ይናገራል ፣ | ፲፮ ፣ ፲፫ |
| ለፊሊጶስ ተናገረ ፣ | ሐዋ. ፰ ፣ ፳፱ |
| ለአገልግሎት ይጠራል ፤ | » ፲፫ ፣ ፪ |
| ይጸልያል ፣ | ሮሜ፣ ፰ ፣ ፳፮ |

## አካል ያለው ሰው በመሆኑ ፤

| | |
|---|---|
| ተዋሸ ፣ | ሐዋ. ፭ ፣ ፫ |
| ተፈተነ ፣ | » ፭ ፣ ፱ |
| ተቃወሙት ፣ | » ፯ ፣ ፶፩ |
| ያዝናል ፣ | ኤፌ. ፬ ፣ ፴ |
| ተሰደበ ፣ | ማቴ. ፲፪፣ ፴፩ |

ከላይ የተጠቀሱትን ጥቅሶች አንዳንዶቹን ባብራራቸው በይበልጥ ሃሳቡን ለመጨበጥና ለመረዳት እንችላለን ። ለምሳሌ በማቴ. ፲፪ ፣ ፴፩ ያለውን ጥቅስ እንውሰድ ፣ «ስለዚህ እላችኋለሁ ኃጢአትና ስድብ ሁሉ ለሰዎች ይሰረይላቸዋል ። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን ለሰደበ አይሰረይለትም» ግልጽና ቀጥተኛ ከሆነው ከዚህ ጥቅስ መንፈስ ቅዱስ አካል እንዳለው ለመረዳት የሚያስቸግር አይደለም ።

፮ ፤ መንፈስ ቅዱስ ምንም እንኳን ከአብና ከወልድ የሚወጣ ቢሆንም በመለኮት ሆነ በባሕርይ ከአብና ከወልድ የሚያንስ አይደለም ። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስን የበታች አድርገን መገመት የለብንም ።

መንፈስ ቅዱስ ከሁለቱ የሥላሴ አካላት ጋር (ከአብና ከወልድ) ባለው ግንኙነት የሚጠራው በሦስተኛ ሥፍራ ነው ። ይህም ማለት በአንደኛ ወይም በሁለተኛ ሥፍራ አይጠራም ማለት ነው ። አብ የመጀመሪያ ሥፍራ አለው ። ምክንያቱም ሁለተኛውን አካል ወልድን ስለሚወልድ ነው ። ወልድ ሥፍራው ሁለተኛ ነው ምክንያቱም አብ ልጄ በማለት ስለሚጠራው ነው ፤ መንፈስ ቅዱስ ሥፍራው ሦስተኛ ነው ። ይህም ከአብና ከወልድ ስለሚወጣ ነው ። የተሰጣቸው ሥፍራ አንዱ ከአንዱ እንደሚበልጥ የሚገልጽ ሳይሆን በመጽሐፍ ቅዱስ ያላቸውን አገላለጽና አቀማመጥ የሚያመለክት ነው ።

የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ ስንመለከት የአብ ፣ የወልድ ፣ የመንፈስ ቅዱስን አገላለጥ ግልጽ ሆኖ እናያለን ። መንፈስ ቅዱስ በሚገባ የተገለጸው ከአብና ከወልድ በኋላ ነው ። ከዘፍጥረት እስከ ክርስቶስ ልደት ሲሰራ ጐልቶ የሚታየው አብ ሲሆን በዘፍጥረት ክብርን ተመልቶ እናየዋለን ። ክርስቶስ ወደዚህ ምድር ሲመጣ የአብ ክብር በእርሱ ላይ ሲያንጸባርቅና ጐልቶ ሲታይ እናያለን ። በዚህ የክርስቶስ ምድራዊ ዘመን መንፈስ ቅዱስ በግልጥ ሲሠራ አልታየም ነገር ግን ኢየሱስ ወደ አባቱ ከአረገ በኋላ መንፈስ ቅዱስ በግልጽ ሲሠራ ጐልቶ ይታያል ። ይህ ከላይ የተመለከትነው ቅደም ተከተል የሚያሳየን በሥላሴ ውስጥ ያለውን ቅደም ተከተል የሚገልጽ መሆኑን ነው ።

መንፈስ ቅዱስ ከሥላሴ ጋር ካለው ግንኙነት አንዱ ከአብና ከወልድ የሚወጣ መንፈስ መሆኑ ነው ። ምንም እንኳን ሁኔታውን በበለጠ ለማስረዳት የሚያስቸግር ቢሆንም በእግዚአብሔር ቃል የተገለጸ ስለሆነ እንቀበለዋለን ።



ምዕራፍ ፫ ፤

# መንፈስ ቅዱስ የተጠራበት ስሞችና ምሳሌዎች ፤

ባለፈው ምዕራፍ እንደ ገለጽኩት የእግዚአብሔር መንፈስ አንድ ቢሆንም በተለያዩ ስሞች መጠራቱን ገልጫለሁ ። ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ስሞች መንፈስ ቅዱስ በአዲስና በብሉይ ኪዳን የተጠራባቸው ስሞች ናቸው ።

## በብሉይ ኪዳን ፤

መንፈስ ቅዱስ መዝ. ፶፩ ፡ ፲፩
መልካም መንፈስ መዝ. ፻፵፫ ፡ ፲ ፤
የፍርድ መንፈስና የሚያቃጥል መንፈስ ኢሳ. ፬ ፡ ፬ ፤
ሰባቱ መናፍስት ኢሳ. ፲፩ ፡ ፪ ፤
የሞገስና የልመና መንፈስ ዘካ. ፲፪ ፡ ፲ ፤

## በአዲስ ኪዳን ፤

አጽናኝ ዮሐ. ፲፬ ፡ ፲፮ ፤
የእውነት መንፈስ ዮሐ. ፲፮ ፡ ፲፫ ፤
የተሰፋ መንፈስ ኤፌ፡ ፩ ፡ ፲፫ ፤
የዘለዓለም መንፈስ ዕብ፡ ፱ ፡ ፲፬ ፤

## የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌዎች ፤

መንፈሳዊው ዓለም የሰው አእምሮ ሊደርስበት የማይችል እጅግ የረቀቀ ነው ። ስለዚህ እግዚአብሔር በቃሉ ሁሉን በምሳሌና በማስረጃ አቅረቦልናል ። ኢየሱስ ራሱን በእረኛ ፣ በመንገድ ፣ በእንጀራ ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት በወይን አትክልት ፣ በዕንቁ ፣ በመረብ ይመስላል ።

እንደዚሁም የመንፈስ ቅዱስ ጠባይና አሠራር ከሰው አዕምሮ በላይ በመሆኑ እግዚአብሔር ድካማችንን በማወቅ መንፈስ ቅዱስን በምሳሌ ያቀርባልናል ። ከምሳሌዎቹም መካከል ውሃ ፣ ነፋስ ፣ ትንፋሽ ፣ እሳት ፣ ዘይት ፣ ርግብ ፣ ማኅተም ናቸው ። እስቲ እያንዳንዳቸውን በአጭሩ እንመልከታቸው ።

፩/ ውሃ ፡— መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስን በብዙ ሥፍራ በውሃ ይመስለዋል ። ይህም የሆነበት ሁለት ምክንያት አለ ። አንደኛ መንፈስ ቅዱስ ለክርስቲያኑ

መንጻትንና መቀደስን ስለሚሰጠው ሁለተኛ ውሃ በዕለታዊ ኑሮአችን ውስጥ ከፍተኛ ሥፍራ ስለአለውና መንፈስ ቅዱስም የሕይወት ምንጭ በመሆኑ ነው ።

የእግዚአብሔር ቃል መንፈስ ቅዱስ መለወጥን እንደሚሰጥና እንደሚቀድስ ያስተምረናል ። ሰው ደግሞ በኃጢአት የተጨማለቀ መሆኑን ይገልጽልናል።ልጆች በጭቃ የተጨማለቀ ሰውነታቸውና ልብሳቸው በውሃ እንደሚጸዳ እንዲሁ መንፈስ ቅዱስ ወደ ኃጢአተኛው ሕይወት መጥቶ የሚያደርገው ተመሳሳይ ነገር ነው ። ከኃጢአት እሥራት ነፃ ያደርገዋል ፣ ልቡን በመለወጥ ይቀድሰዋል ።

ይህ ሃሳብ በመዝሙር ፶ በዳዊት ጸሎት ላይ ግልጽ ሆኖ ይታያል ። «ከበደሌም ፈጽሞ እጠበኝ ከኃጢአቴም አንጻኝ······ በሂሶጵ እርጨኝ እነጻማለሁ ። እጠበኝ ከበረዶም ይልቅ ነጭ እሆናለሁ» ሕዝቅኤልም በሚናገርበት ጊዜ ተመሳሳይ አገላለጥ አለው ። «ጥሩ ውሃንም እረጭባችኋለሁ ፣ እናንተም ትጠራላችሁ ከርኩስታችሁም ሁሉ ፣ ከጣዖቶቻችሁም ሁሉ አጠራችኋለሁ ፤ አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ ፣ አዲስም መንፈስ በውስጣችሁ አኖራለሁ» ሕዝ. ፴፮ ፣ ፳፭—፳፯ ። እንዲሁም ሐዋርያው ጳውሎስ ደግሞ ልደትን «መታጠብ» ከሚለው ሃሳብ ጋር ያያይዘዋል ። «እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን» ቲቶ ፫ ፣ ፭ ከዚህ በላይ በተመለከትናቸው ሦስት ክፍሎች የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ከውሃ ጋር ተዛምዶ አይተናል።ይህ የመንፈስን አዳኝነትና ቀዳሽነት ያሳያል።

የውሃ ጠቃሚነቱ ቆሻሻን ለማስወገድ ብቻ ሳይሆን በዕለት ኑሮአችንም ውስጥ ከፍተኛ ሥፍራ አለው ። ሰው እንስሳት ፣ ተክሎች ያለ ውሃ መኖር አይችሉም ። ጥሩ ምንጭ ብዙ ውሃ ይሰጣል ። ቢቀዳ ሰዎች ቢጠጡለትም ያ ምንጭ ውሃ ከማፍለቅ አያቋርጥም ። ከመልካሙ ምንጭ የሚፈሰው ውሃ ባለፈበትና በፈሰሰበት ደረቁን ሥፍራ ወደ ለምለምነት ፣ የደረቀውን ሣር ወደ አረንጓዴነት ይለውጣል ። ኢየሱስ የመንፈስን ሥራ ከዚህ ጋር በማያያዝ ሲናገር «ማንም የተጠማ ቢኖር ወደኔ ይምጣና ይጠጣ ። በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውሃ ምንጭ ከሆዱ ይፈልቃል ። ይህን በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለ መንፈስ ተናገረ ። ኢየሱስ ገና ስለ አልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበረና» ዮሐ. ፯ ፣ ፴፯—፴፱ በማለት ይናገራል ። እንደ ኢየሱስ አነጋገር አማኙ የማይደርቅ የማያቋርጥ ሕይወት ይኖረዋል ። ይህም ማለትም ምንም ሊያቆመው ሊያቋርጠው የማይችል ሰላምና ደስታ አለው ማለት ነው ። ኢሳያስም በ፵፬ ፣ ፫—፬ የገለጸው ከዚህ የተለየ ትርጉም አይሰጠውም ። «በተጠማ ላይ ውሃን በደረቀም መሬት ላይ ፈሳሾችን አፈስሳለሁና ፣ መንፈስን በዘርህ ላይ በረከቴንም በልጆችህ ላይ አፈሳለሁ ። በፈሳሾችም አጠገብ እንደሚበቅሉ አኻያ ዛፎች በሣር መካከል ይበቅላሉ» መንፈስ ባለበት ሕይወት አለ ፤ ውሃ ለደረቅ መሬት ሕይወት እንደሚሰጥ መንፈስ ቅዱስም ለተጠማች ነፍስ እንዲሁ ነው ። እንግዲህ ውሃ የመንፈስ ቅዱስን ሥራ በሁለት አቅጣጫ ይገልጸዋል ። አንደኛ የሚያነጻና የሚቀድስ መሆኑ ሁለተኛ ሕይወት የሚሰጥ ኃይል መሆኑን ።



፪/ <u>ነፋስ</u> ፣— ኢየሱስ ስለ ዳግም ልደት ለኒቆዲሞስ ለማስረዳት ሲናገር እንዲህ አለ ። «ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል ድምጹንም ትሰማለህ ነገር ግን ከወዴት እንደመጣ ወዴትም እንዲሄድ አታውቅም ። ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ እንዲሁ ነው» ዮሐ. ፫ ፣ ፰ ምሳሌው ግልጽ ነው ። መንፈስ ቅዱስ ሕይወትን ለመለወጥ ሥራውን እንዴት እንደሚሠራ አናውቅም ልንረዳው የማንችል ረቂቅ ነገር ነው ። ነፋስ እንደማይታይና እንደማይጨበጥ መንፈስም እንዲሁ ነው ። የነፋስን የሥራ ውጤት እናያለን ። ኃይሉንም እናውቃለን ። ባሕር ሲናወጥ ፣ ዛፎችን ሲጥል ፣ ቤት ሲገለበጥ ፣ እናያለን ፣ መንፈስ ቅዱስም ኃጢአተኛውን እንዴት እንደሚለውጥ አናውቅም ። ይሁን እንጂ ኃጢአተኛው ተለውጦ እናያለን ።

ከሁሉ ይልቅ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ሁለት የተገለጸው ነፋስ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ መሆኑን ግልጽ ያደርገዋል ። በበዓለ ሃምሳ መንፈስ ቅዱስ ሲወርድ በነፋስ መልክ ነው ። «እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምጽ መጣ ተቀምጠው የነበሩትን ቤት ሁሉ ሞላው» ሐዋ. ፪ ፣ ፪ ። እግዚአብሔር ነፋስን በምሳሌነት የተጠቀመው አንድም ረቂቅ መሆኑን ለማሳየት ነው ።

ሌላው የምንመለከተው የነፋስን ኃይል ነው ፤ ከላይ እንደገለጽኩት ነፋስ ባሕርን እስከ ማናወጥ ከተማን እስከ ማፈራረስ ኃይል አለው ። እንደዚሁም መንፈስ ቅዱስ የኃጢአተኛውን ሕይወት በመለዋወጥና በኃጢአት ላይ ድል በመስጠት ያበረታዋል ። ከዚህም በላይ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለመመስከርና ለተጠራበት አገልግሎት ብርታት ይሰጠዋል ።

፫/ <u>እሳት</u> ፣— ማንኛውም ሰው የእሳት ምሳሌነት በምን አቅጣጫ ለመንፈስ ቅዱስ እንደተሰጠ ይገባዋል ። ምክንያቱም እሳት ኃይል ነው ። በበዓለ ሃምሳ ቀን መንፈስ ቅዱስ ሲወርድ እንደ ዓውሎ ነፋስ ብቻ አልነበረም ፣ ቃሉ እንደሚናገረው «እንደ እሳት የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው ፤ በያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው» ሐዋ. ፪ ፣ ፫ ይህ በላያቸው ላይ የወረደባቸው መንፈስ ዮሐንስ እንዳለው እንደ እሳት ያለ ኃይል ነበር ። «ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል ። እርሱም በእሳት ያጠምቃችኋል» ማቴ. ፫ ፣ ፲፩ ።

ይህ እሳት የሚያጠራ እሳት ነው ። ቁጥር አሥራ ሁለትን ብንመለከት «መንሹ በእጁ ነው አውድማውንም ፈጽሞ ያጠራል ስንዴውንም በጐተራው ይከታል ። ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል» ይላል ። ይህ ጥቅስ መንፈስ ቅዱስ በሕይወታችን ውስጥ ያለውን ኃጢአት እንደሚያቃጥልና አማኙን በቅድስና እንዲኖር ያስችለዋል ።

፬/ <u>ዘይት</u> ፣— አራተኛው የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ዘይት ነው።የዚህ ምሳሌነት የተገኘው ከብሉይ ኪዳን ነው ። ብሉይ ኪዳን በብዙ ቦታ ስለ መቀባት ያስተምራል ። በብሉይ ኪዳን ነብያት ካህናት ነገሥታት ይቀቡ ነበር ። ይህም የሚደረገው በራሳቸው ላይ ዘይት በማፍሰስ ነበር ፤ የዚህ ምሳሌ ፣ የተሰጣቸውን ሥልጣን የሚያመለክትና መንፈስ ቅዱስ በሥራቸው እንደሚረዳቸው ነው ። ስለዚህ ዘይት የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ሆነ ።

ቀደም ብዬ እንዳልኩት የመቀባት ሃሳብ ከብሉይ ተያይዞ ወደ አዲስ ኪዳን የመጣ ነው ። የግሪኩ ቃል ኢየሱስን «ክርስቶስ» ይለዋል ። ይህም የተቀባ ማለት ሲሆን ኢየሱስ እንደ ንጉሥ ፥ እንደ ካህን ፥ እንደ ነቢይ መቀባቱን ያመለክተናል። ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን የነበሩትን ሦስቱንም ሥፍራዎች ይዞ ነበር ማለት ነው። በዮርዳኖስ በዮሐንስ በውሃ ሲጠመቅ በዚያው ሰዓት እግዚአብሔር በመንፈሱ ቀብቶታል ። «የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው ። ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና ለታሠሩትም መፈታትን ፥ ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ የተጠቁትንም ነፃ አወጣ ዘንድ፥የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል» ሉቃ ፬ ፥ ፲፰—፲፱ በማለት ኢየሱስ የትንቢቱን ቃል በመጥቀስ ይናገራል።

ክርስቶስ የሚለው ቃል ክርስቲያን የሚለውን ቃል ይሰጠናል ። ክርስቲያን ማለት የክርስቶስ ተከታይ የሚል ቢሆንም የጥሬ ቃሉን ትርጉም ከተከተልን የሚሰጠን ትርጉም የተቀቡ የሚል ነው ።

በሌላ አንጻር መንፈስ ቅዱስ የዘይት ምሳሌነት የተሰጠው ዘይት በጥንቱ ዘመን እንደ መድኃኒት ስለሚቆጠር ነው ። ይህም በእግዚአብሔር ቃል ተጠቅሶ ይገኛል ። «ከእግር ጫማ አንስቶ እስከ ራስ ድረስ ጤና የለውም ፤ ቁስልና እበጥ ፤ የሚመግልም ነው ፤ አልፈረጠም ፥ አልተጠገነም ፥ በዘይትም አልለዘበም» ኢሳ. ፩ ፥ ፮ ፤ ወደ አዲስ ኪዳን ተመልሰን ስንመለከት የዘይትን መድኃኒትነት የሚገልጽ ጥቅስ እናገኛለን ። «አንድ ሳምራዊ ግን ሲሄድ ወደ እርሱ መጣ ፤ አይቶትም አዘነለት ፥ ቀርቦም ዘይትና የወይን ጠጅ በቁስሎቹ ላይ አፍስሶ አሰራቸው» ሉቃ. ፲ ፥ ፴፫—፴፬ ፤ በእነዚህ ጥቅሶች የምንመለከተው ፥ በፈረጠ ቁስል ላይ ዘይት ቢፈስ እረፍት እንደሚሰጥ ነው ።

እንደዚሁም መንፈስ ቅዱስ እረፍት ላጣው ሕይወት ፥ በኃጢአት ቁስል ለተወረሰች ነፍስ እረፍት ይሰጣል ። መንፈስ ቅዱስ በፈተና ፥ በጭንቀት ፥ ውስጥ ላለ ክርስቲያን ሰላምን ይሰጣል ፤ ለሰላሙም ፍጻሜ የለውም ። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እንደማያቋርጥ እንደሚፈስ ዘይት ነው ።

ርግብ ፥— አራቱም ወንጌላት መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ላይ በርግብ አምሳያ መውረዱን ይነግሩናል ። ወንጌላቱ በወፍ ወይም በሌላ ምሳሌ ሳይሆን ለምን በርግብ ምሳሌ መውረዱን ይነግሩናል ። ነገር ግን ርግብ የንጽሕና ፥ የየዋህነት ፥ የጨዋነት ምልክት መሆኑን እናውቃለን ። ኢየሱስ በማቴዎስ ፲ ፥ ፲፮ ሲናገር «እነሆ እንደ በጐች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ ፤ እንደ እባብ ልባሞች እንደ ርግብ የዋሆች ሁኑ» ኢየሱስ በሌላ ሥፍራ ሲናገር «እኔ የዋህ በልቤም ትሁት ነኝ» ይላል።

ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እንደ ርግብ በላዩ ላይ ሲወርድ ማየቱ የመንፈስ ቅዱስን ጠባይ ብቻ ሳይሆን ኢየሱስንም የመንፈስ ፍሬ የሞላበት መሆኑን ይገልጽልናል ።

ማኅተም ፥— በመንፈስ ቅዱስ ታትመናል ብለን እናምናለን ። ኤፌ፥ ፩ ፥ ፲፫ ፤ ፬ ፥ ፴ ፤ ፪ ቆሮ. ፩ ፥ ፳፪ ይህም የደኅንነታችን ምልክት ነው ። ማኅተም የሥራን ፍጻሜ ፍጹምነትን ፥ ስምምነትን ፥ የዋጋ መከፈልን ፥ ያመለክታል ። ኤር. ፴፪ ፥



፱—፲ መንፈስ ቅዱስ በልባችን ያለ ማኅተም ነው ፤ ይህም የእግዚአብሔር መሆናችንን ፥ በክርስቶስ ደም መገዛታችንን ክርስቶስ በመስቀል ላይ በፈጸመው ሥራ መጽደቃችንን ያመለክታል ። ስለዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ ሲናገር «ለቤዛ ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ አታሳዝኑ» ይላል ።

በእግዚአብሔር ቃል የተጠቀሱ ሌሎችም የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌዎች አሉ። ነገር ግን ከዚህ በላይ ዘርዝሬ ማብራሪያ ያቀረብኩባቸው በቂ ይሆናሉ ብዬ አምናለሁ።

አብራርቼ ገልጫለሁ ። በአብራራሁትም ላይ እንደገለጽኩት የነቢያቱ አገልግሎት በቀጥታ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ነበር ፤ ይህም ነቢያቱ በእግዚአብሔር የተጠሩ መሆናቸውን ይገልጻል ። ፩ ሳሙ. ፫ ፥ ፩—፱ ፤ ነገሥት ቀዳማዊ ፲፰ ፥ ፱ ፤ ኢሳ. ፩ ፥ ፩ ፥ ፮ ፥ ፩ ፥ ኤር. ፩ ፥ ፩። እነዚህ ነቢያት በራሳቸው ስም የተነሱትን ነቢያት በማውገዝ ስለ እውነት መስከሩ ።

በብሉይ ኪዳን የነቢያቱን አገልግሎት ስንመለከት ትንቢት ከመናገር በላይ ሆኖ እናገኘዋለን ። ይህም በፍጹም በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው በመንፈስ ቁጥጥር ሥር ሆነው እናያለን ። ለምሳሌ ሳዖልንና አሽከሮቹን በለዓምን እንመልከት ፦ ፩ ሳሙ. ፲ ፥ ፲ ፤ ፩ ሳሙ. ፲፱ ፥ ፲፰ ፤ ዘኁልቍ ፳፫ ፥ ፭ ፤ ዘኁልቍ ፲፩ ፥ ፳፭ እንደተገለጸው የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል ወርዶባቸው ራሳቸው ተናጋሪዎቹ ሊረዱት ከሚችሉት በላይ በሆነ መንገድ ትንቢት ተናገሩ ።

በአንዳንድ ቦታ በብሉይ ኪዳን «ትንቢት» በሰውየው ላይ መንፈስ ቅዱስ ለመውረድ ምልክት ሆኖ ሠርቷል ። ስለዚህም «የእግዚአብሔርም መንፈስ ወረደበት ። ትንቢትም ተናገረ» የሚለው ሐረግ ተደጋግሞ ይገኛል ። አንዳንድ ሥፍራም የትንቢት ስጦታ አንድ ጊዜ ሠርቶባቸው ሁለተኛ ያልተነበዩ ሰዎች አሉ ፤ ለምሳሌ ሙሴን ይረዱ ዘንድ የተመረጡትን ሰባውን ሰዎች ለመጥቀስ ይቻላል ፤ ነገር ግን ትላልቁ ነቢያት እንደ ሳሙኤል ፥ ኤልያስ ፥ ኢሳይያስና ኤርምያስ የመሳሰሉት ቋሚ የሆነ ጥሪ በመቀበል እግዚአብሔር እስከ ዕድሜያቸው ፍጻሜ ሲጠቀምባቸው እናያለን ። እነዚህ ነቢያት የወደፊቱን የሚናገሩ ብቻ ሳይሆኑ ለእሥራኤል ሕዝብ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚገልጹ ነበሩ ። መልእክታቸው እግዚአብሔር ኃጢአትን የፍርድ መጉዳልን የሚጠላ መሆኑን የሚገልጹ በመሆናቸው በየትኛው ዘመን ለሚኖሩ የሚሆን ነው ።

የትንቢታቸው ዋና ሃሳብ መሢህ ክርስቶስ እንደሚወለድ እንደሚመጣ የሚገልጹ ናቸው ። በዚህም ትንቢታቸው የዳዊት ልጅ የእግዚአብሔር ባርያ በማለት በተለያየ ስም ቢጠሩትም ኢየሱስ በእግዚአብሔር መንፈስ ተቀብቶ እንደሚመጣ ተናግረዋል ። አዲስ ኪዳን እንደሚያስረዳን የነቢያቱ ትንቢት በኢየሱስ ተፈጽሟል ። እርሱ በመጣ ጊዜ የብሉይ ኪዳን አገልግሎቶች ከፍተኛውን ሥፍራ ያዙ ።

### ሐ/ <u>መንፈስ ቅዱስና አማኙ ፤</u>

ብሉይ ኪዳን አልፎ አልፎ መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዱ አማኝ ውስጥ እንዴት እንደሚሠራ ይናገራል ፤ ምንም እንኳ አገላለጹ እንደ አዲስ ኪዳን የተብራራና ግልጽ ባይሆንም አምላኪው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለውን ግንኙነት በመጠኑ ይገልጻል ።

መንፈስ ቅዱስ ከእያንዳንዱ ጋር ስላለው ግንኙነት የሚያስረዳ ከመዝሙር ፩፻፴፱ ፥ ፯ የተሻለ ጥቅስ አይገኝም ፤ ይህም ጥቅስ ስለ ሁለት ነገሮች ይናገራል ። አንደኛ የእግዚአብሔር መንፈስ በሥፍራ ሁሉ እንደሚገኝ ሁለተኛ የእግዚአብሔር መንፈስ ሰውን እንደሚመረምር ፤ ዳዊት እንደሚናገረው በሕይወት ቢኖር ቢሞት ፥



በምድር ቢሆን በሰማይ ፥ በሲኦል ቢሆን በመንግሥተ ሰማያት ከእግዚአብሔር መንፈስ ሊርቅ አይችልም ፤ ሰው ሁለመናው በእግዚአብሔር የታወቀ ነው ። ስለ ዚህም እግዚአብሔር በመንፈሱ አማካኝነት ይመረምረዋል ።

ሌላው መንፈስ ቅዱስ ከአምላኪው ጋር ስላለው ግንኙነት የሚያስረዳ ጥቅስ መዝሙር ፶፩ ፥ ፲—፲፩ ያለው ነው ። በዚህ ምዕራፍ መዝሙረኛው ኃጢአቱን ሲናዘዝ ሰላሙና ደስታው እንዲታደስለት ሲጠይቅ እናነባለን ። ከቍ. ፲—፲፩ ያለውን ስንመለከት አንድ አማኝ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ስላለው ግንኙነት ይገልጻል ፤

«አቤቱ <u>ንጹህ ልብን ፍጠርልኝ</u>
የቀናውንም <u>መንፈስ በውስጤ አድስ</u>
ከፊትህ አትጣለኝ
<u>ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ ላይ አትውሰድብኝ</u>

ከእነዚህ ጥቅሶች ሦስት ነገሮችን እንመለከታለን ። ሦስቱም የመንፈስ ቅዱስን ሥራ የሚገልጹ ናቸው ።

<u>ንጹህ ልብን ፍጠርልኝ</u> ፦ ነቢዩ ኤርምያስ እንደተናገረው ጌታ እግዚአብሔር ለእሥራኤል በገባው ኪዳን መሠረት አዲስ ልብን እንደሚፈጥርላቸው በመንፈሱም አማካኝነት ሕጉን በልቦናቸው እንደሚጽፈው ተናግሮአል ፤ ይህም ዳዊት ንጹህ ልብ ፍጠርልኝ ካለው ጋር የተያያዘ ነው ። ምክንያቱም ዘማሪው እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት አዲስ ልብ እንዲፈጥርለት ጠይቋል ።

<u>የቀናውን መንፈስ በውስጤ አድስ</u> ፦ ከመንፈስ ቅዱስ ሥራ አንዱ ለሰዎች መታደስን መስጠት ነው ። (ኤፌ . ፬ ፥ ፳፫) ዳዊት ይህን መታደስ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት እንዲያገኝ እግዚአብሔርን ይጠይቃል ።

<u>ቅዱስ መንፈስህን ከእኔ አትውሰድብኝ</u> ፦ ከሁሉም የበለጠ ይህ ሐረግ መንፈስ ቅዱስ በዳዊት ሕይወት እንደሚሠራ ይገልጻል ። ዳዊትም የመንፈስ ቅዱስን ሥራ በሕይወቱ ስለተለማመደ በኃጢአት በወደቀበት ጊዜ እግዚአብሔር መንፈሱን ከእርሱ እንዳያርቅበት ይጸልያል ።

መንፈስ ቅዱስ በብሉይኪዳን በአምላኪው ሕይወት ውስጥ እንደሚሠራ ምሳሌ አድርገን የወሰድነው ዳዊትን ነው ። እንደተብራራውም መንፈስ ቅዱስ የሚፈውስ ፥ የሚያነጻ ፥ የሚያድስ ነው ። የመንፈስ ቅዱስን ሥራ በአማኝ ውስጥ (በብሉይ ኪዳን) ከዚህ በበለጠ ለማብራራት ያስቸግራል ። ምክንያቱም በግልጽ አምላኪው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለውን ግንኙነት የሚገልጽ ጥቅሶች ባለመኖራቸው ነው ። ሌላው ቢቀር «መንፈስ ቅዱስ» የሚለው ቃል በብሉይ የተገለጸው ሁለቴ ብቻ ነው ። ቢሆንም መንፈስ ቅዱስ በአማኙና በነቢያቱ ሕይወት እንደሠራ የማያጠራጥርና በፍሬው የሚታይ ነው ።

ይልቁንም የመንፈስ ቅዱስ ተስፋ ግልጽ በሆነ ሁኔታ በኢዩኤል ትንቢት መነገሩ መንፈስ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ሰፋ ያለ ሥፍራ እንዳለው ያስረዳል ። ነቢዩ

ለበት ይመስላል ። ሕዝ. ፴፮ ። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ያለውን ሰው ሊረዳና ሕይወት በመስጠት ሕያው ሊያደርገው የሚችል መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው ። ካለ መንፈስ ቅዱስ ሰው ራሱን ወደ እግዚአብሔር ሊመለስ አይችልም ።

### ሀ/ መንፈስ እንዴት መለወጥን ይሰጣል?

በመጀመሪያ ልንገነዘበው የሚገባ ነገር መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስ በምን ዓይነት ሁኔታ ወይም እንዴት ለሰዎች መለወጥን እንደሚሰጥ አይነግረንም ። ይህ ታላቅ ምስጢር ነው ። ሐዋርያው ጳውሎስ «ሕይወታችሁ በክርስቶስ ውስጥ ተሰ ውሮአል» ይላል ። ቆላ. ፫ ፡ ፫ ። ክርስቶስ ወደ ሰው ሕይወት እንዴት እንደሚገባና መለወጥን እንደሚሰጥ ለማወቅ አስቸጋሪ ነው ። ነገር ግን ለአማኙ መለወጥ ፡ አዲስ ፍጥረት መሆንን ሰጥቶት እናያለን ። በአጠቃላይ ሥራውን ውጤቱን እናያለን ማለት ነው ።

ጌታ ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ እንዳለው የነፋስን ድምጽ ትሰማለህ ፡ ይነፍስማል ፤ አዋራን ሲያነሳ ዛፎችን ሲንቀሳቀስ ታያለህ ፡ ነገር ግን ከወዴት እንደመጣ ፡ ወዴት እንደሚሄድ አታውቅም ። በአጠቃላይ አነጋገሩ ውጤቱን ታያለህ ንፋስን ግን አታ የውም ማለት ነው ። የመንፈስ ቅዱስም ሥራ እንዲሁ ነው ። የመንፈስ ቅዱስን ሥራ ምስጢራዊ የሚያደርገው ዋና ምክንያት መንፈስ ቅዱስም ሆነ የሰው ነፍስ የማይታይና የማይጨበጥ መሆናቸው ነው ። እንግዲህ መሠረታዊውን ነገር ከተረዳን መንፈስ ቅዱስ አዲስ ልደትን በመስጠት ላይ በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጡትን አንዳንድ ነገሮች እንመልከት ።

፩ ፤ መለወጥ ወይም አዲስ ልደት ከመቅጽበት የሚሆን ነው ። አዲስ ልደት ቀስ በቀስ የሚሆን ወይም ወር እየቆጠረ የሚሆን አይደለም ። እንዲህ ያለ የመን ፈስ ሥራ ስለሌለ አንድ ሰው እንደ ተለወጠ አዲስ ልደትን አግኝቷል ወይም አል ተለወጠም ። መካከለኛ ሥፍራ የለም ስለዚህ አንድ ሰው እየተለወጥኩ ነው ወይም እየተወለድኩ ነው ለማለት አይችልም ።

፪ ፤ መንፈስ ቅዱስ ወደ አንድ ሰው በመጣ ጊዜ እውነትን መግለጥ ብቻ ሳይ ሆን ለዚያ ሰው መለወጥን ይሰጠዋል ፤ መንፈስ ለሰው የአነጋገርን ፡ የአስተሳሰብን የሥራን መለወጥ ብቻ አይደለም ። ነገር ግን ወደሰውየው ውስጣዊ ሕይወት ወደ መንፈሱ በመግባት መሠረታዊ የሆነ ለውጥ ይሰጠዋል ። ጌታ ኢየሱስ በማርቆስ ፯ ፡ ፳፩—፳፫ ባለው እንደተናገረው ከውስጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ ሐሳብ ፡ ዝሙት ፡ መስረቅ ፡ መግደል ፡ ምንዝርነት ፡ መጐምጀት ፡ ክፋት ፡ ተንኰል ፡ መዳራት ፡ ምቀኝነት ፡ ስድብ ፡ ትዕቢት ፡ ስንፍና ናቸው ። ይህ ክፉ ሁሉ ከውስጥ ይወጣል ሰውንም ያረክሰዋል ። እንግዲህ እንደ ጌታ አነጋገር ይህ ሁሉ ከሰው ውስጣዊ ሕይወት የሚፈልቅ ነው ፤ እንግዲህ መንፈስ ቅዱስ አንድን ሰው ለመቀየርና ሕይወቱን ለመለወጥ መንፈስ ወደ ሰውየው ውስጣዊ ሕይወት በመግባት መሠረታዊ ለውጥን ይሰጠዋል ።



፫ ፤ ደኅንነት ወይም አዲስ ልደት ሙሉ ለሙሉ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው ። አንድ ሕፃን በማሕፀን ሲፀነስ በራሱ ውሳኔ ካለመኖር ወደ መኖር ልምጣ በማለት አይደለም ። መቼ እንደሚወለድ ቤተሰቦቹ ሊያደርጉት ስላለው ጥንቃቄ ለመናገር አይችልም ፤ እንዲሁ አዲስ ልደት ሙሉ ለሙሉ የመንፈስ ሥራ ነው ። ለዚህ ነው ዮሐንስ ሲናገር «ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ አል ተወለዱም» የሚለው ።

### ለ/ የአዲስ ልደት ውጤት ፤

ነፋስን ማየት አንችልም ሥራውን ግን እናያለን ፤ መንፈስ ቅዱስ እንዴት ሰዎችን እንደሚለውጥ አናውቅም ነገር ግን ሥራውን ፡ ፍሬውን እናያለን ። ውጤቱም አሮጌው ሰው ወጥቶ በአዲስ ሰው መተካቱ ፤ መራራው ሕይወት ጣፋጭ ነገር ሲያፈልቅ ፡ እሾህማው ሕይወት ወይን ሲያፈራ መታየቱ ነው ። ይህም የመ ንፈሰ ፍሬ ነው ፤ ሐዋርያው ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች በጻፈው የሥጋ ፍሬ የመንፈስ ፍሬ በማለት ዝርዝሩን ይናገራል ። ስለ መንፈስ ፍሬ ሲናገር ፍቅር ፡ ደስታ ፡ ሰላም ፡ ትዕግሥት ፡ ቸርነት ፡ በጐነት ፡ ዕምነት ፡ የዋህነት ፡ ራስን መግዛት ገላ ፭ ፡ ፳፪ ይላል ፤ እነዚህን ሁሉ ሰው በገዛ ራሱ ሊያገኝ አይችልም ። ነገር ግን በውስጡ የእግ ዚአብሔር መንፈስ ሲያድር እነዚህን ሁሉ ያፈራል ። ጌታ ኢየሱስ ስለ ሀሰተኞችና ስለ እውነተኞች ሲናገር በፍሬያቸው ትለዮአቸዋላችሁ ይላል ። ስለዚህም ሲናገር «ዛፍ ሁሉ ከፍሬው ይታወቃል ከእሾህ በለስ አይለቅሙም ፡ ከአጣጥ ቁጥቋጥም ወይን አይቆርጡም» ይላል ሉቃ. ፮ ፡ ፵፬ ።

አዲስ ልደት በሰውየው ሕይወት አዲስ መሆንን ይሰጠዋል ። ፪ ቆሮ. ፭ ፡ ፲፯ ። ይህም ማለት የዚያን ሰው መሠረታዊ ጠባዮች (ኃጢአት ያልሆኑ) ይለውጣል ፤ ማለት አይደለም ። ይህም የሚለወጠው ሰው ማንነቱ ሳይቀየር ክርስቲያን ይሆ ናል ። ነገር ግን የኃጢአት አገልጋይ የነበረው ሰው ሮሜ. ፮. ፳ የጽድቅ አገልጋይ ይሆናል ማለት ነው ። ይህም አማኙ በመንፈስ ቁጥጥር ሥር እንዲሆን ያደርገዋል ፤ የተለወጠ ሰው በመንፈስ ይራመዳል ፡ በመንፈስ ይኖራል ፡ በመንፈስ ይመራል ፡ በመንፈስ ይሞላል ። ሮሜ. ፰ ፡ ፬ ፤ ገላ. ፭ ፡ ፲፮ ፤ ሮሜ ፰ ፡ ፲፬ ፤ ኤፌ. ፮ ፡ ፲፰ ።

ይህ ሰው በመለወጡ ፍጹም ሆነ ማለት አይደለም ነገር ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ኃይል ይኖረዋል ። ክርስቶስንም እየመሰለ በማደግ ወደ ሙላቱ ይደርሳል ። ክርስቶስን በሕይወቱ እያንጸባረቀ ሲኖር የእግዚአብሔር ቤተሰብ መሆኑ ይታወቃል ፤ ፍሬ የማይታይበት ደኅንነት አጠራጣሪ ነው ። ጌታ ኢየሱስ እንዳስተ ማረው የመንፈስ ፍሬ እጅግ አስፈላጊና የደኅንነት ሚዛን ነው ።

## ምዕራፍ ፮ ፤

# ኢየሱስና መንፈስ ቅዱስ ፤

ኢየሱስ በምድራዊ ዘመኑ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የነበረውን ግንኙነት ለመረዳት ስለ ኢየሱስ ትክክለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ አስተሳሰብ በአእምሮአችን እንዲቀረጽ ያስፈልጋል ።

እርሱ የሥላሴ ሁለተኛው አካል ነው ። አብ ልጄ ብሎ ስለሚጠራው «ልጅ» ተብሎ ይጠራል ። በባሕርዩም ፍጹም አምላክ ፣ ዘላለማዊ ፣ ሁሉን ቻይ ፣ ኃያል ሁሉን አዋቂ ፣ በየትም ሥፍራ የሚገኝ ነው ። ጊዜው በደረሰ ጊዜ ይህ ዘላለማዊው አምላክ ከሴት ተወለደ ሥጋ ለበሰ ፣ እንደኛም ሰው ሆነ ፣ ይህም ሲሆን አምላክዊው ባሕርይ ከእርሱ ጋር እንዳለ በተጨማሪ ሰው ሆነ ማለት ነው ። ኢየሱስ በዓለም ከኖሩት ሰዎች የተለየ ነበር ። ይህም ሰው ሆኖ ፍጹም አምላክ መሆኑ ነበር ።

እንግዲህ ምንም እንኳን አምላክ ቢሆን የሰው ባሕርይ ተካፋይ ስለነበር መንፈስ ቅዱስ አስፈልጉት ነበር ። አዲስ ኪዳንን ስናነብ በግልጽ የምንመለከተው ከመወለዱ እስከ ማረጉ ባለው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ከኢየሱስ ጋር ይሠራ ነበር ። የጠነከረ ግንኙነትም ነበረው ። ይህንንም በዝርዝር እንደሚከተለው እንመለከታለን ።

### ሀ/ የኢየሱስ ሥጋ መልበስ ፤

መንፈስ ቅዱስ ገና ኢየሱስ በሚጸነስበት ጊዜ አስፈልጎ ነበር ። በወንጌሎቹ ግልጽ ሆኖ እንደሚታየው «ማርያም ከመንፈስ ቅዱስ ጸንሳ ተገኘች» ማቴ. ፩ ፡ ፲፰ መለአኩ ገብርኤልም ወደ ማርያም መጥቶ ያላት «መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህም ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል» ሉቃ. ፩ ፡ ፴፭ ። እንግዲህ ከዚህ ጥቅስ እንደ ምንመለከተው ኢየሱስ በማርያም ማኅጸን እንዲጸነስ ያደረገው መንፈስ ቅዱስ ነው ። ይህ የሰው አእምሮ የማይቀበለው ቢሆንም የመጀመሪያው የአዲስ ኪዳን ተአምር በመሆኑ እንቀበለዋለን ።

ምንም እንኳን ሥራው የመንፈስ ቅዱስ ቢሆንም ሌላው የሥላሴ ክፍል አብ ሥፍራ የለውም ማለት አይደለም ። ቀደም ብለን በፍጥረት ሥራ አብ ፣ ወልድ ፣ መንፈስ ቅዱስም ሦስቱም እንደተባበሩ እንዲሁም ኢየሱስ መጸነስ የእግዚአብሔር ሥራ ነው ። ለዚህም ኢየሱስ ለአባቱ «መሥዋዕትንና መባን አልወደድክም ሥጋን ግን አዘጋጀህልኝ» ዕብ. ፲ ፡ ፭ ያለው አብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር መተባበሩን ይገልጽልናል ፤ ዕብ. ፲ ፡ ፭ በቀላል አማርኛ ሲብራራ እግዚአብሔር አብ የኢየሱስን ሥጋ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት አዘጋጀ ማለት ነው ። ኢየሱስም በማርያም ማኅጸን በማደሩ ሥፍራ አለው ፤ ይህም በፈቃዱ ለአብ በመታዘዙ ዓለምን በመውደዱ ወደ



ዚህ ዓለም መጣ ። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን ሲገልጽልን «እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አል ቆጠረውም ነገር ግን የባርያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ ፣ በምስሉም እንደሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ» ፊልጵ. ፪ ፡ ፮—፯ ።

የኢየሱስ ክርስቶስ ከመንፈስ ቅዱስ መጸነስ እጅግ ከፍተኛና በጣም አስፈላጊ ዶክትሪን ነው ። ኢየሱስ ከኃጢአት ነፃ መሆኑን የምናስረዳበት ዋና ማስረጃ ነው ። ኢየሱስ ከመንፈስ ቅዱስ በመጸነስ ከአዳማዊ የኃጢአት ተፈጥሮ ነፃ ካልሆነ በስ ተቀር «አዳኝ» ሊሆን አይችልም ። ሰው ሲወለድ የኃጢአት ተፈጥሮ ይዞ ነው ፤ ክር ስቶስ ግን በመንፈስ ስለ ተጸነሰ ፍጹም ቅዱስ ነው ። ሰው በመሆኑ በነገር ሁሉ ተፈትኖአል ። ነገር ግን በአንዱ ኃጢአት እንኳን አልወደቀም ። ዕብ. ፬ ፡ ፲፭ ፤ ኃጢአት በውስጡ አልነበረም ፪ ቆሮ. ፭ ፡ ፳፩ ፤ ኃጢአትም አልሠራም ፩ ጴጥ. ፪ ፡ ፳፪ ፤ ነቀፋና ተንኮል ያልተገኘበት በግ ነው ፩ ጴጥ. ፩ ፡ ፲፱ ፤ እንዲሁም ቅዱስ ያለነቀፋ ንጹህ ከኃጢአተኞች የተለየ ነው ዕብ. ፯ ፡ ፳፮ ።

እንግዲህ ሃሳቡን ለማጠቃለል ኢየሱስ በተፈጥሮ ቅዱስ የአዳም ኃጢአት ያልተላለፈበት የኃጢአት ተፈጥሮም ያልነካው ነበር ። ከዚህ የምንመለከተው መን ፈስ ቅዱስ ከኢየሱስ መወለድ ከፍተኛ ሥፍራ እንደነበረው ነው ።

### ለ/ የኢየሱስ እድገት ፤

ሉቃስ በወንጌሉ መንፈስ ቅዱስ ከኢየሱስ እድገት ጋር የተያያዘ መሆኑን ሲነግረን «ሕፃኑም አደገ ። ጥበብም ሞልቶበት በመንፈስ ጠነከረ ። የእግዚአብሔርም ጸጋ በእርሱ ላይ ነበረ» ይላል ሉቃ. ፪ ፡ ፵ ፤ ሉቃስ ሕፃኑም አደገ ሲል በሥጋ ፣ በመ ንፈስ ፣ በእውቀት ያለውን ሁሉ ያጠቃልላል ። ይህንንም ሉቃስ በቁጥር ፶፪ ላይ ሲናገር «ኢየሱስ ደግሞ በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት አደገ» ይላል ። ኢየሱስ በሥጋው ማንኛውም ሕፃን በሚያልፍበት የእድገት ደረጃ ዎች ማለፍ ነበረበት ። በዚያው መጠን በመንፈስ ያድግ ነበር ፤ ይህም ማለት መለ ኮታዊነቱ ያድግ ነበር ማለት አይደለም ። ምክንያቱም የመለኮትም ምልአት ከማኅ ጸን ጀምሮ በርሱ ላይ ነበር ። ነገር ግን ሰው በመሆኑ የመንፈስ እድገት አስፈለገው ። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን ኢየሱስ ሙሉ ሰው ሆኖ በሚያገለግልበት ጊዜ የዳ ግም ምጽአቱን ጊዜ እንኳን ለይቶ አያውቀውም ነበር ። ኢሳያስ መንፈስ ዘወትር ከኢየሱስ እንደ ማይለይ ሲናገር «ከእሴይ ግንድ በትር ይወጣል ። ከሥሩም ቁጥቋጦ ያፈራል ። የእግዚአብሔር መንፈስ የጥበብና የማስተዋል መንፈስ የምክርና የኃይል መንፈስ የምክርና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ያርፍበታል ።» ኢሳ. ፲፩ ፡ ፩—፪

### ሐ/ የኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ መቀባት ፤

ሉቃስ እንደሚነግረን ምንም እንኳን ኢየሱስ ከሕፃንነት መንፈስ ቅዱስ ያረ ፈበት ቢሆንና በማስተዋል ፣ በእውቀት እያደገ ቢሄድም አገልግሎቱን ከመጀመሩ በፊት በመንፈስ ቅዱስ መቀባት አስፈልጉት ነበር ።

፭ ፤ ይህ ጥምቀት ለሁሉ አማኞች የተሰጠ እንጂ በተለይ የጥቂቶች ብቻ አይደለም ።

፮ ፤ ይህ ጥምቀት አማኙን በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የክርስቶስ አካል ያደርገዋል ። በአዲስ ኪዳን እንደምናነበው አዲስ ልደትን ያገኘ ሰው ወዲያው መንፈስ ቅዱስን ተቀብሏል ። ይህም መንፈስ የክርስቶስ አካል ያደርገዋል ።

እዚህ ላይ ጌታን የተቀበሉ በመንፈስ ተጠምቀዋል ከተባለ ሁለተኛው ልምምድ ከዳኅንነት በኋላ የምናገኘው ምን ሥፍራ ይኖረዋል? የሚል ጥያቄ ይኖራል ። እርግጥ ቀደም ብዬ የጠቀስኩት ሁለተኛው ክፍል ይህን ጥያቄ አይቀበለውም ። ምክንያቱም ሁለተኛ ጥምቀት የለም ስለሚሉ ነው ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ልምምድ «ሙላት» ይለዋል ። በኋላም እንደምንመለከተው ይህ ሙላት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የሚከተሉት ሲሆን ከእነዚህም መካከል አንዱ በቋንቋ መጸለይ ነው ።

«በመጠመቅ» ና በ«መሞላት» መካከል ያለውን ልዩነት ካየን በሁለተኛው ልምምድ ላይ ስላለው ልዩነት ለመግለጽ እፈልጋለሁ ። በመንፈስ ቅዱስ መሞላትና በልሳን መጸለይ የማይቀበሉ ክፍሎች እምነት «አንድ ጥምቀት ብዙ መሞላት» የሚለው ነው ። ይህም ማለት ጌታን ስንቀበል በመንፈስ ተጠምቀናል ። በየጊዜው ግን በመንፈስ እንሞላለን የሚል ነው ። ነገር ግን የሚያሳዝነው ብዙዎች አንድም ቀን እንኳን በመንፈስ አለመሞላታቸው ነው ። እዚህ ላይ እግዚአብሔር በፈቀደ ጊዜ ይሙላኝ እንጂ ልጠይቀው አይገባኝም ወይም አያስፈልገኝም የሚሉ አሉ ። ይህን የእግዚአብሔር ቃል እንዲመልሰው ማድረግ በቂ ነው ። «ለምኑ ይሰጣችሁማል ፤ ፈልጉ ታገኙማላችሁ ፤ መዝጊያን አንኳኩ ይከፈትላችኋል. . . በሰማይ ያለው አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣቸው? ሉቃ. (፲፩ ፥ ፱ ፤ ፲፫) ከዚህ ቃል እንደምንረዳው የመለመን ፤ የመፈለግ ፤ የማንኳኳት ኃላፊነት አለብን ይህም እግዚአብሔርን መጠበቅ ማለት ነው ። ሐዋርያትም ከጌታ የሱስ የተሰጣቸው ትዕዛዝ በኢየሩሳሌም ሆነው መንፈስ ቅዱስን እንዲጠብቁ ነው ። ሉቃ. ፳፬ ፥ ፵፱ ።

ነገር ግን ሰዎች አንድ ጥምቀት ብዙ መሞላት የሚለውን በዶክትሪን ደረጃ የተቀበሉት ቢሆንም ጌታ እንዲሞላቸው በየጊዜው የጠየቁበትና የተሞሉበት ጊዜ የለም ። እንግዲህ ይህን ሁለተኛ ልምምድ «ጥምቀት» እንበለው «ሙላት» ወደ ልምምድ እስካልመጣን ድረስ ለመመስከር ለማገልገል ኃይል አይኖረንም ። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደምንመለከተው ከየትኛውም ቤተ ክርስቲያን ይሁኑ እግዚአብሔር የተጠቀመባቸው ሰዎች በመንፈስ የሚሞሉ ነበሩ ፤ ከእነዚህም መካከል ለመጥቀስ ያህል ፊኒ ፥ ዲ ፥ ኤል ሙዲ ፥ ቶሪ በቂ ማስረጃ ናቸው ። ዛሬ ስንት አገልጋዮች ናቸው እንደ ደረቅ አጥንት ሆነው ሕይወት የሌለው ስብከት የሚያቀርቡ? ምክንያቱ አንድና ግልጽ ነው ። ሕይወት ከሚሰጠው መንፈስ ቅዱስ መራቃቸው ነው ።



ለ/ <u>የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ለሐዋርያት ብቻ የተሰጡ አይደሉም</u> ፤

በሁለተኛ ደረጃ የመንፈስ ቅዱስን ሙላት የሚቃወሙ ክፍሎች የሚያቀርቡት ምክንያት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ለመጀመሪያ ይቱ ቤተ ክርስቲያን ብቻ የተሰጡ በመሆናቸው ስጦታዎቹ በሃያኛው ክፍለ ዘመን ላለችው ቤተ ክርስቲያን አይሰጥም የሚል ነው ። ይህ አነጋገር ለሰው አእምሮ እንደሚመች የተቀነባበረ እንጂ የመጽሐፍ ቅዱስ ድጋፍ ያለው አይደለም ። ስለ መንፈስ ቅዱስ በተሰጡት ተስፋዎች ሆነ በክርስቶስ ትምህርት ስጦታዎቹ ለተወሰነ ዘመን ብቻ እንደሚሠሩ የተገለጠበት ቦታ የለም ። ይልቁን የእግዚአብሔር ቃል የሚለው «እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል ፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል» ነው ። ዮሐ. ፲፬ ፥ ፲፪ ። ጌታ እዚህ ላይ ለይቶ ለሐዋርያት አልተናገረም ነገር ግን <u>«በእኔ የሚያምን»</u> ነው የሚለው ፤ ጌታ ኢየሱስ በማር. ፲፮ ፥ ፲፯ «ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል» በማለት ስለ ልዩ ቋንቋ ፥ ስለፈውስ ፥ ስለ አጋንንት ማስወጣት ይናገራል ፥ ይህ ሥልጣን ለሐዋርያት ብቻ የተሰጠ እንደ ሆነ አይናገርም ። ነገር ግን <u>«ያመኑትንም»</u> በማለት ይናገራል ።

መጽሐፍ ቅዱስ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ እውነት ነው እንቀበላለን የሚሉ ብዙዎች ናቸው ነገር ግን ከላይ የተጠቀሱትን ጥቅሶች እንዳሉ የሚቀበሉ ጥቂቶች ናቸው ። ማለት ለጥቅሶቹ ማብራሪያና ትርጉም በመስጠት ያልፏቸዋል ማለት ነው ። ለምሳሌ በዮሐንስ ፲፬ ፥ ፲፪ ያለውን ጥቅስ የክርስቶስ ሥራ መፈወስ ፥ ታምር ማድረግ ብቻ ሳይሆን ማስተማርና መስበክ ጭምር ነው ። ስለዚህ ማስተማርና መስበክን ማለቱ ነው የሚሉ አሉ ፤ እርግጥ ነው መሠረተ ሃሳቡ ትክክል ነው የክርስቶስ ሥራ ማስተማርና መስበክ ነበር ይሁን እንጂ መፈወስና ተአምራትንም የሚጨምር ነበር ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን እንደጻፈው ጌታ ኢየሱስ ለቤተ ክርስቲያን አምስት የአገልግሎት ስጦታዎችን ሰጥቷል ። እነርሱም ሐዋርያት ፥ ነቢያት ፤ ወንጌል ሰባኪዎች ፤ እረኞችና አስተማሪዎች ናቸው ። ከእነዚህ መካከል አንዱ ነቢያት ናቸው ፤ የወንጌል ሰባኪዎች ፥ የእረኞች የአስተማሪዎች አገልግሎት ዛሬም እንዳለ ካመንን ፥ ለምን የነቢያትን ገንጥለን እናወጣዋለን? ምናልባት የነቢይነትን አገልግሎት የሚቀበሉም ቢኖሩ ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ባለማያያዝ ነው ማለትም «ትንቢት» ለሚለው ቃል መስበክ የሚል ትርጉም በመስጠት ነው ፤ ምንም እንኳን ይህ አነጋገር እንደ ሐዋርያት ሥራ ፲፭ ፥ ፴፪ መሠረት እውነት ያዘለ ቢሆንም የነቢይ ትርጉም በዚህ አያቆምም ። ምክንያቱም ነቢያት በመገለጥ ስጦታዎች የተሞሉ ናቸውና ።

በዚህ አንጻር ይህን ከተመለከትን ወደተነሳንበት ሃሳብ በመመለስ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታዎች ዋጋ ቢስ ያደርጋል ከሚባሉት ጥቅሶች አንዱ በአንደኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ አሥራ ሦስት የሚገኘውን እንመልከት ። ቃሉም እንዲህ ይላል ። «ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም ትንቢት ቢሆን ግን ይሻራል ፥ ልሳኖች ቢሆኑ ይቀራሉ ፥

በሐዋርያት ሥራ በአምስት ሥፍራዎች ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ሲሞሉ እናያለን ። በሦስቱ በልሳን እንደተናገሩ በግልጽ ስናነብ በሁለቱ ግን እንደሦስቱ ሳይሆን በልዩ መንገድ ተገልጾ እናነባለን ። የመጀመሪያው ሦስቱ በበዓለ ሃምሳ ሐዋ. ፪ ፥ ፬ ፤ በቆርኖሊዎስ ቤት ፥ ፲ ፥ ፵፬—፵፮ ፤ በኤፌሶን ፲፱ ፥ ፮ ፤ ጳውሎስ ሐናንያ እጁን ጭኖበት ሐዋ. ፱ ፥ ፲፯ ፤ ፩ ቆሮ. ፲፬ ፥ ፲፰ ፤ አምስተኛው በሰማርያ ፰ ፥ ፲፬—፲፯ ፤ በፊሊጶስ ስብከት ብዙዎች ከተለወጡ በኋላ ጴጥሮስና ዮሐንስ በሰማርያ የሆነውን በሰሙ ጊዜ ወደ ሰማርያ መጥተው ለመንፈስ ቅዱስ ጸለዩላቸው ። በዚህ ሥፍራ በልሳን መናገር በቀጥታ አልተገለጸም ቢሆንም ቃሉ ሰምዖን ስለተባለው ሰው ሲናገር «ሲሞንም በሐዋርያት እጅ መጫን መንፈስ ቅዱስ እንዲሰጥ ባየ ጊዜ ገንዘብ አመጣላቸውና እጄን የምጭንበት ሁሉ መንፈስ ቅዱስን ይቀበል ዘንድ ለእኔ ደግሞ ይህን ሥልጣን ስጡኝ» አለ ። ፲፰—፲፱ ፤ ስሞን ያየው ነገር ሌላ ሳይሆን ሰዎች በልሳን ሲናገሩ ነው ። ኢየሱስ በማር. ፲፮ ፥ ፲፯—፲፰ አማኞች ከሚከተላቸው ምልክት አንዱ በልዩ ቋንቋ መናገር መሆኑን ይገልጻል ፣

> «የሚያምኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል ፦
>
> በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ ፥ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ ፤
>
> እባቦችን ይይዛሉ ፥ የሚገድልም ነገር ቢጠጡ አይጎዳቸውም ፥ እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ» ማር. ፲፮ ፥ ፲፯—፲፰ ።

ስለዚህ እንደ እግዚአብሔር ቃል የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ምልክቱ በልሳን መናገር ነው ፤ ከመንፈስ ቅዱስ ሙላት ብዙ የጸጋ ስጦታዎች የሚገለጹ ሲሆን ልሳን ግን ቀዳሚ ምልክት ነው ።

## ፭/ በልሳን ሳልናገር በመንፈስ ቅዱስ ለመሞላት አልችልም?

ከባድና መስቀለኛ ጥያቄ ነው ። ከባድና መስቀለኛ የሚያደርገው ከላይ በሰጠሁት የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ በመንፈስ የተሞሉ ሁሉ በልሳን እንደተናገሩ የገለጽኩ ሲሆን ባለፈው የቤተክርስቲያን ታሪክ ሆነ ዛሬም በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው በልሳን የማይናገሩ ክርስቲያኖች አልፎ አልፎ መገኘታቸው ነው ። እኔ በግሌ ሁለትና ሦስት የሚሆኑ አገልጋዮች አውቃለሁ የእግዚአብሔር ኃይልና የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በሕይወታቸው የሚታይ ፥ ነገር ግን በልሳን አይናገሩም ። አንደኛውን ወንድም እንዳናገርሁት «የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በእኔ እንዳለ በሕይወቴ ተገልጦ ሲሠራ አይቻለሁ ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ «በልሳን የሚናገር ራሱን ያንጻል» ስለሚል የዚህ በረከት ተካፋይ እንድሆን በልሳን እንድናገር እየጸለይኩ ነው» ብሏል ።

ከላይ እንደዘረዘርኩት ሰዎች በልሳን ሳይናገሩ በመንፈስ ቅዱስ ሊሞሉ እንደሚችሉ ገልጫለሁ ፥ ይሁን እንጂ እንዲህ ያለውን ሙላት አናስተምርም ፥ አናደፋፍርም ።



## ፮/ እንዴት በመንፈስ ቅዱስ መሞላት እችላለሁ?

ሰዎች መንፈስ ቅዱስን በተለያየ መንገድ ስለሚቀበሉ ሰው ሠራሽ ፎርሙላ ልናወጣለት አንችልም ። በሐዋርያት ሥራ እንደምንመለከተው ሐዋርያት በጸሎት ላይ ሳሉ በመንፈስ ተሞሉ ፥ ሐዋ. ፪ ፥ ፬ ፤ ጳውሎስ ሐናንያ እጁን በጫነበት ጊዜ በመንፈስ ተሞላ ሐዋ. ፱ ፥ ፲፯ ፤ ፩ ቆሮ. ፲፬ ፥ ፲፰ ፤ ቆርኖሊዎስና አብረውት የነበሩ የጴጥሮስን ስብከት ሲያደምጡ ተሞሉ ፤ ዛሬም መንፈስ ቅዱስ እንደወደደ በተለያየ መንገድ ወደ ሰዎች ይመጣል ። ይህንንም «ምስክርነት» ከሚለው ርዕስ ሥር የአንዳንድ ሰዎችን ምስክርነት በማንበብ ለመረዳት እንችላለን ።

ይሁን እንጂ መሠረታዊ የሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ የተደገፉ መመሪያዎች አሉ ። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት የፈለገ ሰው ከሁሉ በፊት ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኝበት ጊዜና ሥፍራ እንዲኖረው ያስፈልጋል ። ብዙዎች በዕለት ጸሎታቸው ስለዚህ ጉዳይ ጠቅሰው ከመጸለይ በቀር የተወሰነ ጊዜ ወስደው በእግዚአብሔር ፊት የቀረቡበት ጊዜ የለም ። ይህን ልዩ ጊዜ የምናሳልፈው የጸጥታ ሥፍራ እስካገኘን ድረስ በቤትም ሆነ በቤተክርስቲያን ልዩነት የለውም ። በሁለተኛ ደረጃ ስለ መንፈስ ቅዱስ የተሰጡትን የተስፋ ቃሎች ደጋግሞ ማንበብ ነው ። እነዚህ የተስፋ ቃሎች ስለልሳን እምነት ከመፍጠራቸውም እግዚአብሔርን በመታመን እንድንጠባበቅ ይረዱናል ። ሌላው አስፈላጊ ነጥብ በጸሎት መንፈስ ቅዱስን መጋበዝ ነው ። መንፈስ ቅዱስን እየጋበዝን ልንጠራጠር አይገባንም ። አንዳንድ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ከተሞሉ በኋላ እንኳን በፍርሃትና በጥርጥር ስለተያዙ አፋቸውን ከፍተው እግዚአብሔር በሰጣቸው ልሳን አይናገሩም ። እንግዲህ እምነታችን በሥራ የሚገለጸው እዚህ ላይ ነው ። ሐዋ. ፪ ፥ ፬ የሚለው «በመንፈስ ተሞሉ» «በልሳኖችም ተናገሩ» ነው ። መንፈስ ከወረደባቸው በኋላ የመናገሩ ኃላፊነት የእነርሱ እንጂ የመንፈስ ቅዱስ አልነበረም ። አንዳንዶች ከተሞሉ በኋላ አንድን ፊደል ብቻ በመደጋገም ይናገራሉ ። ይህ ከፍርሃትና ከጥርጥ የሆነ እንጂ መንፈስ የሰጣቸው ቋንቋ በውስጣቸው እንደታሠረ ነው ። ስለዚህ በመንፈስ ቅዱስ ከተሞላን በኋላ በእምነት በመናገር ወደ ሙላት በረከት እንመጣለን ።

ከላይ እንደገለጽኩት መንፈስ ቅዱስ እንደ ወደደ በተለያየ መንገድ ወደ ሰዎች ይመጣል ። አንዳንዶች ሲጸልዩ ሌሎች በመኝታቸው ውስጥ እንዳሉ አንዳንዶችም ሥራ እየሠሩ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተዋል ። ዛሬ የልብዎን መዘጋጀት በማየት መንፈስ ቅዱስ በማንኛውም ሥፍራና ሁኔታ ወደርሶ ሊመጣ ይችላል ፤ ከዚህ በታች በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ የአንዳንድ ክርስቲያኖች ምስክርነት አቀርባለሁ ። ልምዳቸው ዛሬ ለብዙዎች በረከት እንደሚሆን አምናለሁ ።

## መ/ ምስክርነት ፤

ጸሐፊው የራሱን ምስክርነት በመስጠት ይጀምራል ። የዛሬ አሥራ አንድ ዓመት በሕይወቴ የተፈጸመውን ምንም ጊዜ የማነሳው በአዲስ ስሜት ነው ። ቀኑ ቅዳሜ ወደ አሥራ አንድ ሰዓት አካባቢ ነው ፥ ከጓደኛዬ ጋር ከቤት መንፈሳዊ ነገሮችን ስንወያይ ቆይተን ወደቤቱ መሄጃው ሰዓት ስለደረሰ ለመሄድ ተነሳ ልሸኝህ በማለት

አያምጠው ነበር ። ከዚያም ከተማሪዎች የመኝታ ቤት ጀርባ ተንበርክኬ እጸልይ ጀመር ፣ ወዲያው ጌታ እንደተናገረኝ በመንፈስ ቅዱስ አጠመቀኝ ። በዚህ ጊዜ አቶ ዘለቀን በሰውነትህ ላይ የእግዚአብሔር ኃይል ተሰምቶህ ነበር? ብዬ ለጠየኩት ጥያቄ በአንድ ዓረፍተ ነገር ሲመልስልኝ ፣ «እንደ ኤሌክትሪክ ኃይል ከላይ እስከታች ድረስ ወረረኝ» አለኝ ። ነገር ግን በልሳን የተናገርኩት በመንፈስ ቅዱስ በተሞላሁ ማግሥት ነው ። በማለት ስለመንፈስ ቅዱስ ሙላት ያለውን ምስክርነት ያመመልኝ ።

በእውነት ዛሬ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት የብዙ ሰዎችን ምስክርነት ለመጻፍ ይቻላል ፤ እግዚአብሔር ዛሬም ለሚቀርቡት መንፈስ ቅዱስን በማፍሰስ ስለራሱ ይመሰክራል ።



ምዕራፍ ፱ ፤

# የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ለምን ይጠቅማል?

በዚህ ምዕራፍ ለመናገር የምፈልገው ስለ መሠረታዊ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ዶክትሪን አይደለም ፤ ነገር ግን ይህ ምዕራፍ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በአንድ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ የሚያመጣውን ለውጥና የሚሰጠውን ጥቅም የሚያብራራ ይሆናል ። ስለዚህ ይህ ገለጻ አንድ ሰው ጌታን በተቀበለ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ከሚያገኘው ልምምድ የተለየ ይሆናል ። ይህን ከተረዳንና ካስተዋልን የመንፈስ ቅዱስ ሙላት የሚሰጠውን ጥቅም እንመልከት ።

የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ለክርስቲያኑ ኃይል ይሰጠዋል ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመንፈስ ቅዱስን ሙላት ከኃይል ጋር በማያያዝ ይናገራል ። «እነሆም አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ» ሉቃ. ፳፬ ፣ ፵፱ ፤ ይህ ኃይል የሚለው ካልተብራራ በስተቀር የምንመለከተው በአንድ አቅጣጫ ብቻ ይሆናል ።

፩. የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በኃጢአት ላይ ኃይል እንዲኖረውና ክርስቲያኑ የድል ሕይወት እንዲመላለስ ያደርገዋል ። ብዙ ሰዎች ጌታን እየወደዱ ሳሉ በኃጢአት እየተሸነፉ የሚመላለሱት ድካም በተሞላበት ሕይወት ነው ። ያ የተሸነፉበት ኃጢአት እግዚአብሔርን እንደማያስደስተው ቢያውቁም ኃጢአትን ለመቃወም ወይም ላለማድረግ ኃይል አይኖራቸውም ። ነገር ግን እንዲህ ያለው ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ በሚሞላበት ጊዜ የሚሞላው በኃይል በመሆኑ በሚቸገርበትና በሚወድቅበት ኃጢአት ኃይልና ድል ያገኛል ። ይህም ማለት ክርስቲያኑ የቅድስና ሕይወት እንዲኖር ያስችለዋል ።

፪. ጌታ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ «እስከ ዓለም ፍጻሜ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ» ሲል ካለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት ይህን ተልእኮ ሊፈጽሙት እንደማይችሉ ስለሚያውቅ «ኃይል እስክትለብሱ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ» ሲል ተናገራቸው።የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ክርስቲያኑ የምስክርነት ሕይወት እንዲኖረው ያደርጋል ። ብዙ ክርስቲያኖች ስለጌታ ክብር ቢመሰክሩ ደስ ይላቸዋል ። ነገር ግን ኃይል አጥተው አንደበታቸውን መክፈት አቅቷቸው ይቸገራሉ ። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በላያቸው ሲወርድ ፍርሃታቸውን ወደ ድፍረት በመለወጥ እንዲመሰክሩ ይረዳቸዋል ። መንፈስ ቅዱስ በምስክር ሕይወት የሚያመጣው ለውጥ ድፍረትን መስጠት ብቻ ሳይሆን መስካሪው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተሞላ ቃላትን በመናገር የሰውየው ሕይወት በቀላሉ እንዲነካ ያደርጋል ።

ድውያንን ፈወሱ አጋንንትን አወጡ ። ዛሬ በመንፈስ ቅዱስ ከተሞሉ በኋላ የነፍሳት ፍቅር ይዟቸው በአዲስ ኃይል አገልግሎታቸውን የሰጡ በሀገራችን አሉ ። ከእነ ዚህም መካከል አንዱ እስቲ የሚሰጡትን ምስክርነት እንመልከት ።

አቶ ካሣ አጋፋሪ «ወደ መንፈስ ቅዱስ ሙላት ከመምጣቴ በፊት ያሳለፍኩት ሕይወት ሆነ የሰጠሁት አገልግሎት የሚያረካ አልነበረም ይላል ። እዘምር ነበር ፣ እሰብክም ነበር ይሁን ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ሳደርግ እንጂ ወጥቼ ስለ ክርስቶስ አልመሰከርኩም ። ምክንያቱም ኃይልና ድፍረት ስለ አልነበረኝ ነው ።

በዚህ ዓይነት የማያረካ ሕይወት ውስጥ እንዳለሁ ለትምህርት ወደ ባሕር ዳር ፖሊቴክኒክ ሄድኩ ። በዚያ ሥፍራ ሕይወታቸው የሚማርክ ክርስቲያኖች ጋር ተገናኘሁ ፣ በዚህ ጊዜ ስለ እኔ ክርስትና ራሴን መጠየቅ ጀመርኩ ። ቃሉን በማንበብና በአካባቢዬ ያሉትን ክርስቲያኖች ሕይወት በመመልከት ያለሁት በደረቅ ሕይወት ውስጥ መሆኑን ተገነዘብኩ ። እነዚህ ክርስቲያኖች በትምህርት ቤት ውስጥ ተገናኝተው የሚጸናኑበት የስብሰባ ጊዜ ነበራቸው አብሬአቸው እሰበሰብ ጀመር ። ነገር ግን አንድ ቀን ያደረግነው ስብሰባ እጅግ ለየት ያለና በሕይወቴ ታላቅ ሥፍራ የምሰጠው ነው ። ይህ ስብሰባ ከሌሎቹ ሁሉ የሚለየው ሁላችን በመንፈስ ቅዱስ አሳሳቢነት ኃጢአታችንን መናዘዛችን ነው ፣ ቃላት ሊገልጸው በማይችል ሁኔታ ለአምስት ሰዓት ኃጢአታችንን ስንናዘዝ መንፈስ ቅዱስ ለአንድ በረከት ያዘጋጀን እንደነበር አያጠራጥርም ።

ከዚህ በኋላ ነው ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት ከቃሉ በመረዳት መጸለይ የጀመርነው ። ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት በመጸለይ ላይ እንዳለን የዓመቱ የትምህርት ጊዜ በማለቁ ትምህርት ቤት ስለተዘጋ ወደ ናዝሬት ከተማ ሄድኩ ። በዚያም ጊዜ ከባሕር ዳር የበለጠ ታላቅ ነገር በናዝሬት ክርስቲያኖች ላይ አየሁ ፣ ወጣቶቹ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው በልሳን ሲናገሩ ፣ እግዚአብሔርን በመንፈስና በእውነት ሲያመልኩ ሳይ በሕይወታቸው መባረክ ብቻ ሳይሆን እኔም የዚህ በረከት ተካፋይ መሆን እንዳለብኝ ተረዳሁ ። ስለዚህም እንዲጸለዩልኝ ጠይቄ ብዙ ጊዜ ተጸልዮልኝ አልተሞላሁም ። ቢሆንም ስራመድ ስቀመጥ ፣ ስሠራም አስብ የነበረው ስለ መንፈስ ቅዱስ ነበር ። በዚህ ሁኔታ እንዳለሁ አዋሳ የሚደረገውን ዓመታዊ ኰንፍራንስ ለመካፈል ሄድኩ ፣ በዚያ በድንቅ አኳኋን እግዚአብሔር በመንፈስ ሞላኝ ።

ከዚያ በኋላ የሰጠሁትን አገልግሎት ከፊተኛው ጋር ሳወዳድረው ትልቅ ልዩነት አያለሁ ፣ ይህ ብቻ ሳይሆን በግል ለመመስከር የድል ሕይወት ለመመላለስ መንፈስ ቅዱስ አስችሎኛል» በማለት አቶ ካሣ ምስክርነቱን ይደመድማል ።

በመጨረሻ ለመጥቀስ የምፈልገው የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ኢየሱስን እንደሚያከብር ነው ። ብዙ ክርስቲያኖች ኢየሱስን እንደ አስተማሪ ፣ ጓደኛ ፣ እረዳት አድርገው ይቀበሉት እንጂ የሕይወታቸው ጌታና ገዢ አድርገው አልተቀበሉም ። በመንፈስ ቅዱስ ሙላትና ጌታ ኢየሱስን የሕይወታችን ገዢና ጌታ አድርጐ በመቀበል መካከል ትልቅ ግንኙነት አለ ። ኢየሱስ ስለዚህ ሲናገር «እርሱ (መንፈስ



ቅዱስ) ያከብረኛል ። ከእኔ የሆነውንም ወስዶ ለእናንተ ያስተውቃችኋል» አለ ። ዮሐ. ፲፮ ፥ ፲፬ ። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ባለን እረክተን ጌታ ኢየሱስን የሕይወታታችን ገዢ እንድናደርገው ይረዳናል ።

አገልግሎቴን በመንፈስ ቅዱስ ሙላት ያልጀመርኩ ቢሆን ኖሮ ዛሬ ወዳለሁበት የሕይወት ደረጃ እደርሳለሁ ብዬ አልልም ፤— መንፈስ ቅዱስ በሰጠኝ እርካታ ብቻ ነው ስለ ጌታ ሁሉን እንደ ረብ ለመቁጠር የቻልኩትና በየጊዜው በፊቴ የሚቆሙትን ምድራዊ ነገሮች መስዋዕት ለማድረግ ያስቻለኝ መንፈስ ቅዱስ ነው ።

የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ጥቅሙ ይህና ይህ ነው ብሎ ለመናገር ቢያስፈልግ ራሱን የቻለ አንድ መጽሐፍ ይወጣዋል ። ምናልባት ይህን ዝርዝር ካነበብክ በኋላ እነዚህ ሁሉ ዝርዝር ስሰጥ እኔ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የለኝም? መንፈስ አይመራኝም? መንፈስ ቅዱስ ለእኔስ ቃሉን አይገልጽልኝም? የሚል ጥያቄዎች ይኖራሉ። እነኝህ ጥያቄዎች የሚቀርቡት በመንፈስ ቅዱስ ሙላት በማያምኑ ክርስቲያኖች ነው ። ቀደም ብዬ ጌታን በተቀበሉና በመንፈስ በተሞሉ መካከል ያለውን ልዩነት ገልጫለሁ ። ጥያቄውን በአጭሩ ለማጠቃለል ያህል እነዚህ ሁሉ ነጥቦች ወይም የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች ጌታን በተቀበለ ክርስቲያን ሕይወት ሊታዩ ይችላሉ ። ነገር ግን በሙላት በግልጽ የሚታዩት በመንፈስ ቅዱስ ከተሞላ በኋላ ነው ።

## ምዕራፍ ፲ ፤

# የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች

ክርስቲያኖች በመንፈስ ቅዱስ ከተሞሉ በኋላ ወዲያው ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ማሰብ ይጀምራሉ ። ይህም ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ አሳሳቢነት ነው ። መንፈስ ቅዱስ ወደ ሰዎች ሕይወት ሲመጣ ስጦታዎችን ይዞ ነው ። ስጦታ የሚለው ቃል በግሪክ «ካሪስማ» የሚል ነው ። ሌላው ተመሳሳይ ትርጉም ያለው መገለጥ የሚለው ሲሆን የግሪኩ ቃል «ፋኒሮሲስ» የሚል ቃል ነው ።

«ስጦታ» የሚለው ቃል የጸጋ ስጦታዎች የተሻለን ወይም ጥሩዎች ስለሆንን የሚሰጡን ሳይሆን እግዚአብሔር ለልጆቹ የሚሰጠው የጸጋ ስጦታ መሆኑን ይገልጽልናል ። ስጦታ ከእግዚአብሔርር ጋር ያለንን የልጅነት ግንኙነት የሚገልጽ ነው ። ወላጆች ለልጆቻቸው ስጦታ የሚሰጡት ከሌሎች የተሻሉ ጥሩዎች ስለሆኑ ሳይሆን ልጆቻቸው በመሆናቸው ብቻ ነው ። መገለጥ የሚለው ቃል ማሳየት ፣ ማሳወቅ ፣ መግለጥ የሚል ትርጉም ይሰጠዋል ። እነዚህ ሁለት ቃላት እግዚአብሔር በልጆቹ የሚገልጸውን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ግልጽ ያደርጉልናል ። ይህን ሙላት የተቀበልን ክርስቲያኖች ልንገነዘበው የሚገባን ፣ ጌታ እነዚህን ስጦታዎች የሰጠን የእግዚአብሔርን ፍቅር ለሰዎች እንድንገልጽ ነው ።

እግዚአብሔር የመንፈስ ቅዱስን ስጦታዎች ለማንም ለግል መጠቀሚያ አልሰጠም ። ነገር ግን ለቤተክርስቲያን መታነጽያና ፤ መገንቢያ ይሆን ዘንድ ሰጥቷል ። አንድ ክርስቲያን እያደገና በሕይወቱ እየጐለመሰ ሲሄድ ስጦታዎች በሕይወቱ እየተገለጡ ይሄዳሉ ። ይህ ክርስቲያን ሌሎችም ወደዚህ ሙላት እንዲገቡ ማደፋፈር ይኖርበታል እንጂ ሰዎች ወደ እርሱ ብቻ እንዳያተኩሩ ሊጠነቀቅ ይገባዋል ። እግዚአብሔር እንዲጠቀምባቸው የሚፈልጉ ሁሉ እግዚአብሔርን ማድመጥ ይኖርባቸዋል ። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በሕይወታቸው ሊሠራ ሲጀምር የሚሳሳቱ ሊኖሩ ይችላሉ ። ነገር ግን ይህ ክርስቲያኑን ሆነ በአካባቢው ያሉትን ሊያስደነግጣቸው አይገባም ። ምክንያቱም ስጦታዎቹ ፍጹም ቢሆኑም ፍጹም የሆነ ሰው ስለሌለ ነው ። ስለዚህ በስጦታዎች ማደግና መጐልመስ እንዳለ መገንዘብ አለብን ።

ሌላው ልንገነዘበው የሚገባ ነገር ስጦታዎች አንድ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት ሆነ ቅድስና መለኪያ አለመሆናቸውን ነው ። ሮሜ. ፲፩ ፡ ፳፱ ላይ እንደተጻፈው «እግዚአብሔር በጸጋው ስጦታና በመጠራቱ አይጸጸትም» ስጦታዎችን ክርስቲያኑ በድካምና በጥረቱ ያገኛቸው ባለመሆናቸው በሕይወቱ የመንፈስ ፍሬ እንዳለ ማየቱ ትክክለኛ ነው ። ክርስቲያኖች ሰጭውን ጌታ እንጂ ስጦታዎችን አንከተልም ። ስጦታዎች እንደ እግዚአብሔር ቃል ሲገለጡ እጅግ ያማሩ ናቸው ። የእግዚአብሔርም ሕዝብ ከስጦታዎቹ በመጠቀም ይጽናናል ፣ ይባረካል ፣ ይታነጻል ። እዚህ ላይ ከሁለቱ ስህተቶች መጠንቀቅ ይኖርብናል ። አንደኛ



ስጦታዎችን ከእግዚአብሔር ቃል ውጭ መጠቀም ፣ ሁለተኛ ስጦታዎችን በመቃወም ከቤተ ክርስቲያን አለመጥፋትና አለመናቅ ናቸው ። «መንፈስን አታጥፉ ፣ ትንቢትን አትናቁ ፣ ሁሉን ፈትኑ መልካሙንም ያዙ ከማናቸውም ዓይነት ክፉ ነገር ራቁ» ፩ ተሰሎ. ፭ ፣ ፲፱—፳፪ ።

እንግዲህ ወደ ዋናው ሃሳብ እንምጣና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች እነማናቸው ስንል ዝርዝራቸውን በ፩ ቆሮ. ፲፪ ላይ እናገኛለን ። ከዚህ በታች ያለው የስጦታዎች ዝርዝር አቀማመጥ በአንደኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ ፲፪ እንደተዘረዘረው ሳይሆን ለጥናት እንደሚያመች አስቀምጬዋለሁ ።

ሀ የመነዳት ወይም የትንቢት ስጦታዎች ፤

፩. የልሳናት ስጦታ (ትክክለኛውን ትርጉም ለማግኘት የእንግሊዝኛውን መጽሐፍ ቅዱስ አንብብ)
፪. የመተርጐም ስጦታ
፫. የትንቢት ስጦታ ፤

ለ የመገለጥ ስጦታዎች ፤

፩. መናፍስትን የመለየት ስጦታ ፤
፪. እውቀትን የመናገር ስጦታ
፫. ጥበብን የመናገር ስጦታ ፤

ሐ የኃይል ስጦታዎች ፤

፩. የፈውስ ስጦታዎች (ትክክለኛውን ትርጉም ለማግኘት የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ ተመልከት)
፪. ተአምራትን የማድረግ ስጦታ
፫. የእምነት ስጦታ ፤

ከላይ ከተዘረዘሩት ስጦታዎች መካከል ሰባቱ በብሉይ ኪዳን ሠርተዋል ። ሁለቱ በብሉይ ኪዳን ያልተገለጹት በልሳናት መናገርና ፣ የመተርጐም ስጦታዎች ናቸው ። እግዚአብሔር አስቀድሞ በነቢያቱ ሕይወት በሚያስደንቅ ሁኔታ ይሠራ ነበር ፤ ቢሆንም በክርስቶስ ደም የተዋጀችው ቤተ ክርስቲያን በብሉይ ስለሌለች ስጦታዎቹ በአንድ ሰው በኩል ብቻ የሚሠሩ ነበሩ ፤ ስለዚህም በየዘመኑ የተነሱትን ነቢያት መጥቀስ በቂ ነው ። ሙሴ ፣ ኢያሱ ፣ ኤልያስ ፣ ኢልሳዕ እንዲሁም ሌሎቹ ።

እነዚህ ሁሉ ተልእኳቸውን እስኪፈጽሙ ስጦታዎች ሠርተውባቸዋል ። ነገር ግን ለጉባዔ የተሰጡ አልነበሩም ። ስለዚህ በብሉይ ኪዳን የስጦታዎች አጠቃቀም መምሪያ ወይም ፕሪንስፐል ተጽፎ አናይም ፣ ምክንያቱም አሕዛብ በክርስቶስ አስታራቂነት የርስቱ ተካፋዮች እንዲሆኑ አልተጠሩምና ፤ ያለ አሕዛብ መጠራት ቤተ ክርስቲያን ሙላት እንደማይኖራት ከሩቅ የወሰነ እግዚአብሔር እስከ በዓለ ሃምሳ ቀን መንፈሱን አላፈሰሰም ። ክርስቶስ ደሙን በመስቀል አፍስሶ ቤተ ክርስቲያንን ከዋጀ በኋላ በመንፈስ ቅዱስ መሠረታት ያን ጊዜ በሙላትና በኃይል በመ

ንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሽልማት ለራሱም ቅድስትና ነውር የሌለባት ቤተ ክርስቲያን መሠረተ ። ስለዚህ በተሻለውና በበለጠው ኪዳን ውስጥ በመሆናችን እግዚአብሔርን ልናመስግነው ይገባል ። «የምታዩትን የሚያዩ ዓይኖች ብጹዓን ናቸው ።» እላችኋለሁና እናንተ የምታዩትን ብዙዎች ነብያትና ነገሥታት ሊያዩ ወደዱ አላዩምም ፤ የምትሰሙትንም ሊሰሙ ወደው አልሰሙም» አለ ። (ሉቃ. ፲ ፣ ፳፫—፳፬) እግዚአብሔር ይመስገን ፣ ዛሬ ይህ ሙላት ለእያንዳንዳችን የተሰጠ እንጂ ለአንድ ሰው ወይም ለጥቂቶች የተሰጠ አይደለም ። ክርስቶስ ያላቸው ሁሉ ሰማያዊ በረከት ሁሉ የእነርሱ ነው ።

## ፩/ <u>የመነዳት ወይም የትንቢት ስጦታዎች</u> ፤

ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በየተራ በተከፈሉበት አርእስት ሥር እንመለከታቸዋለን ። ከዚህ አርእስት ሥር ስለ ልሳናት ፣ መተርጐምና ትንቢት ስጦታዎች እንመለከታለን ።

እነዚህ ስጦታዎች በሀገራችን ባለው የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ሥፍራ የሚሰጣቸው ስለሆኑ ከሌሎች ስጦታዎች ይልቅ አብልጠን ልንነጋገርባቸው ያስፈልጋል ። በልሳናት መናገር ከዘጠኙ ስጦታዎች አንደኛው በመሆኑ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ፲፪ በሰጠው ዝርዝር ላይ ይገኛል ። በመንፈስ ቅዱስ አማኞች መካከል ስለዚህ ስጦታ የተለያየ ትርጉም ይሰጣል ፤ አንዳንዶች ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ በተሞሉ ጊዜ በልሳን አይናገሩም ፣ ነገር ግን ስጦታ በመሆኑ የሚሰጣቸው አሉ ይላሉ ። ሌሎችም የለም በመንፈስ ቅዱስ የሚሞሉ ሁሉ በልሳን ይናገራሉ ፣ ነገር ግን አንዳንዶች በልዩ ልሳኖች የመናገር ስጦታ ይሰጣቸዋል ፣ ይህም መጀመሪያ በመንፈስ ቅዱስ ሲሞሉ ከሚሰጣቸው ሌላ ነው ይላሉ ። ሃሳቡን ለመግለጽ እንጂ ሁለቱም ወገኖች በልሳን መናገር የሚለውን ትምህርት የሚቀበሉ በመሆኑ ችግር የለውም ።

### <u>የመተርጐም ስጦታ</u> ፤

በልሳናት የመናገር ስጦታ ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም ሊሰጥ የሚችለው ሲተረጐም ብቻ ነው ። በመንፈስ ቅዱስ በተሞላን ጊዜ የምንቀበለው ራሳችንን ለማነጽ የሚጠቅም ነው ። «በልሳን የሚናገር ራሱን ያንጻል» ፩ ቆሮ. ፲፬ ፣ ፬ ነገር ግን በልሳ ሳኖች የሚናገር ለጉባዔ ይናገራል ። ለዚያውም የሚተረጉምለት ቢኖር ወይም ራሱ ቢተረጉም ነው ። ስለዚህ ሐዋርያው ጳውሎስ በልሳን የሚናገር እንዲተረጉም ይጸልይ ይላል ። ዛሬ በሀገራችን ባለው እንቅስቃሴ የመተርጐም ስጦታ እንደሚገባ ሲሠራ አይታይም ። ይህም የሚያሳየው ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው በልሳን ሲናገሩ በትንሹ እንደሚረኩና በጸጋ ስጦታዎች እንደማያድጉ ነው ። ሐዋርያው ጳውሎስ «በልሳን የሚናገር እንዲተረጉም ይጸልይ» ሲል የጉባዔውንና የማኅበሩን ጥቅም በመመልከት ነው ። በቍጥር ፳ መጨረሻ ላይ ስለዚህ ሲናገር «ማኅበሩ ይታነጽ ዘንድ ንግግሩን ባይተረጉም በልሳኖች ከሚናገር ትንቢት የሚናገር ይበልጣል»



ይላል ። እዚህ ላይ ማስተዋል የሚኖርብን ሐዋርያው ጳውሎስ የሚመለከተው የጉባዔውን ጥቅም ነው ። ብዙዎቻችን ስጦታው የተሰጠን ማኅበሩን ለማገልገል ፣ ለጉባዔው መታነጽያ መሆኑን እንዘነጋለን ። ይህም የሚታየው በጉባዔው ስብሰባ ላይ ነው ። ለራሳችን በዝግታና ሌላውን በማይረብሽ ሁኔታ ልንጸልይ ሲገባን ምዕመንን ስናውክና ስንረብሽ እንታያለን ። በልሳኖች መናገር ምላት የሚኖረው ሲተረጐም ብቻ ነው ። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የመተርጐም ስጦታ እንዲሠራ አጥብቀው መጸለይና ማደፋፈር ይኖርባቸዋል ። የመተርጐም ስጦታ ለብዙዎች በረከትና የጸሎት መልስ አምጥቷል ።

ምንም ጊዜ ቢሆን <u>ደጋግሜ ብናገር ደስ የሚለኝ ስጦታዎቹ ለማኅበሩ ጥቅም የተሰጡ መሆናቸውን ነው ።</u> ሐዋርያው ጳውሎስ ደጋግሞ በአሥራ አራተኛው ምዕራፍ (፩ኛ ቆሮ) እንደሚገልጸው ማንኛውም መገለጥ ለቤተ ክርስቲያን እንደሚጠቅም ሆኖ መቅረብ እንዳለበት ነው ። በቍጥር ፳፮ ላይ ሲናገር «በምትሰበሰቡበት ጊዜ ለእያንዳንዱ መዝሙር አለው ፣ ትምህርት አለው ፣ መግለጥ አለው ፣ በልሳን መናገር አለው ፣ መተርጐም አለው ፤ <u>«ሁሉ ለማነጽ ይሁን»</u> ይላል «በልሳን መናገር አለው» የሚለውን በትክክል ልንተረጉመው ይገባል ፤ ይህ «በልሳን መናገር» በጉባዔው መካከል የምንናገረው ሲሆን መልእክት የያዘ ነው ። ስለዚህ ከግላዊ ጸሎት ለየት ያለ ነው ። ወዲያው መልእክቱ በልሳን ከተሰጠ በኋላ የሚተረጉመው መልእክቱን ለጉባዔው ያቀርባል ። ትርጉሙ በሚሰጥበት ጊዜ ጉባዔው መታነጽ ብቻ ሳይሆን ችግሩ የሚፈታለት ጸሎቱ የሚመለሰለት ሰው ሊኖር ይችላል ።

በልሳን የሚናገሩ ሰዎች በዓለም ውስጥ በሚገኝ ቋንቋ እንደሚናገሩ መረዳት ይኖርብናል ይህም በበዓለ ሃምሳ ቀን በሚገባ ተገልጧል «እያንዳንዱ በገዛ ቋንቋው ሲናገር ይሰማ ስለነበር የሚሉትን አጡ» ሐዋ. ፪ ፣ ፮ ። ዛሬም ይህን የመሰለ ሁኔታ ይታያል ። ከእነዚህ መካከል ለምስክር ያህል አንድ አቀርባለሁ ። አንድ ወጣት በጃፓን ሀገር ለሥራ በቆየበት ጊዜ አንዲት ጃፓናዊት ያገባል ። ይህ ወጣት ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጌታን በመቀበል ክርስቲያን ይሆናል ። ሚስቱ በዚህ ቅር ይላትና በመካከላቸው በየጊዜው ክርክር ይነሳል ። እርስዋ የቡድሀ እምነት ተከታይ ስትሆን እምነቷን አጠንክራ የያዘች ነበረች ። ባልዋ ለጸሎት በሚንበረከክበት ጊዜ እርሷም የቡድሃ ጸሎቷን ታደርስ ነበር ።

ከእለታት አንድ ቀን በዚያው አካባቢ የምትኖር ክርስቲያን ሴት ወደነዚህ ወጣት ባልና ሚስት ቤት መጣች ። ሰዓቱም የጸሎት ሰዓት ስለነበር ከእግዚአብሔር ቃል ከተነጋገሩ በኋላ ለጸሎት ተንበረከኩ ። በዚህ ጊዜ ጃፓናዊቷ ወጣት ከባሏ ጐን ተንበርክካ የቡድሃ ጸሎቷን ታደርስ ጀመር ። ጥቂት ከጸለዩ በኋላ ክርስቲያኗ ሴት በልሳን መናገር ጀመሩ ። ጥቂት እንደጸለዩ ጃፓናዊቷ ወጣት በድንጋጤና በመደነቅ ባሏን ሰማኝ ፣ ይህች ሴት የምትናገረው በጃፓንኛ ቋንቋ ነው ። የምትናገረውም ለኔ ነው ። ቋንቋውም ፍጹም ጥራት ያለው በመቅደስ የምንጠቀምበት ጃፓንኛ ነው በማለት ተርበተበተች ። ባሏ አትኩሮ ሲመለከታት ንግግሯን በመቀጠል ፣ ቡድሃ እስከ ዛሬ ምንም አልጠቀመሽ ኢየሱስን ለምን አትሞክሪም አለችኝ» አለ

ችው ። ከዚህ ተአምራዊና ኃይለኛ ድርጊት በኋላ ይህች ሴት ክርስቲያን መሆኗ የማያጠራጥር ነው ። በእርግጥ ክርስቲያን ሆነች ። ዛሬ ከባሏ ጋር በመተባበር የእግዚአብሔርን ታላቅነት ለሰዎች ሁሉ ትናገራለች ።

ይህ በመተርጐም ስጦታ አማካኝነት የተገኘ ፍሬ ባይሆንም በልሳን የተሰጠው መልእክት በዚህች ሴት ሕይወት ውስጥ ትርጉም አግኝቶ ፍሬ አፍርቷል ። በዚህ አንፃር ልገልጸው የሚገባ ነገር ቢኖር የመተርጐም ስጦታ ያለው ሰው ትርጉሙ እንዴት ወደ ክርስቲያኑ እንደሚመጣ መነጋገሩ አስፈላጊ ይመስለኛል ። የልሳን ትርጉም ስጦታው ወዳለው ክርስቲያን እንዴት ይመጣል?

ከሁሉ በፊት መገንዘብ የሚኖርብን የመተርጐም ስጦታ ያለው ክርስቲያን በፈለገው ጊዜ ወይም ሰዎች በልሳን በተናገሩ ጊዜ ትርጉሙ ወደርሱ አይመጣም ፤ በልሳን መልእክት ሲሰጥ መንፈስ መገለጥን ሲሰጠው ብቻ ይተረጉማል ። ከሁሉ በፊት ልንገነዘበውና ልንጠነቀቅበት የሚገባ ጉዳይ ነው ። ይህን ከተረዳን የመተርጉም ስጦታ ምን እንደሆነና እንዴት ትርጉሙ ስጦታው ወዳለው ክርስቲያን እንደሚመጣ ነጥብ በነጥብ አቀርባለሁ ።

፩. «በልሳናት የተነገረውን መተርጐም» የሚለው ስጦታ አስተርጓሚ ማለት አይደለም ። ይህም እንግሊዘኛ ችሎታ ያለው ሰው ሌላውን እንግሊዝኛ ተናጋሪ ወደ አማርኛ እንደሚያስተረጉመው ማለት አይደለም ።

፪. ስጦታው ወዳለው ክርስቲያን ትርጉም ወደ አእምሮው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ሊመጣ ይችላል ። ይህም ማለት የመጀመሪያ ሦስት ወይም አራት ቃላት ብቻ ሊሰጡት ይችላሉ ። በዚያን ጊዜ ክርስቲያኑ በእምነት የተሰጠውን ሦስትና አራት ቃላት መናገር ሲጀምር የተቀረው መልእክት ወደ ሕይወቱ ይፈሳል ።

፫. ትርጉሙ በምሳሌ ወይም የመልእክቱ ሃሳብ ወደ አእምሮው ሊመጣ ይችላል ። እዚህ ላይ እንድንገነዘበው የሚያስፈልግ አንድ ነገር አለ ። ስጦታው ያለው ክርስቲያን ሲተረጉም በዘልማድ የሚጠቀምባቸው ብዙ ጊዜ ከእርሱ የምንሰማቸውን ቃላት ሊጠቀም ይችላል ። በዚህ ጊዜ የተናገረው ከስሜቱ ነው በሚል ትችት እንዳንያዝ እንጠንቀቅ ። ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ ለተርጓሚው የሰጠው የመልእክቱን ሃሳብ ነው ። ስለዚህ ክርስቲያኑ በራሱ ቃላት ትርጉሙን ያመጣል ።

፬. መልእክቱ ወደ ጉባኤ በልሳን ከመምጣቱ በፊት ተርጓሚው ትርጉሙ ቀደም ብሎ ይሰጠዋል ። በዚህ ጊዜ ከራሱ ወይም ከእግዚአብሔር የመጣ መልእክት መሆኑን በጸሎት በሚፈትንበት ወቅት በልሳን መልእክት ይመጣል ። በዚህ ጊዜ በመንፈስ በመሞላት ኃይልና እምነት በማግኘት ትርጉሙን ይሰጣል ።

፭. አንዳንድ ጊዜ በልሳን የተሰጠው መልእክት አጭር ሆኖ ሳለ ትርጉም ረጅም ሲሆን አንዳንዶች ይገረማሉ ። ለዚህ ብዙ ምክንያት መስጠት ይቻላል ፤ ከእነዚህም መካከል ተርጓሚው መንፈስ የሰጠውን ትርጉም ወይም ሃሳብ ለመግለጽ ረጅም ዓረፍተ ነገር ስለሚጠቀም ነው ። ወይም ተርጓሚው በትንቢት መንፈስ በመሞላት



አዲስ መገለጥን አግኝቶ ይሆናል ። እነዚህ ዋና ምክንያቶች ሲሆኑ ሌሎቹም መንፈስ ብቻ ሊገልጸው የሚችል ምክንያቶች ይኖራሉ ።

የትርጉም ስጦታ ዓላማ ከትንቢት ስጦታ የተለየ አይደለም ። ትርጉሙ ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ ፣ ለመምከር ፣ ለማጽናናት የሚነገር ነው ። ፩ ቆሮ. ፲፬ ፣ ፫—፭ ፤ ከዚህም በተለይ በብዙ መንገድ እግዚአብሔር ሊሠራ ይችላል ። ዋናውና ተፈላጊው መልእክቱ ለእግዚአብሔር ጉባዔ የሚጠቅም መሆኑ ነው ።

ስለዚህ ስጦታ ከተነጋገርን አንድ ልሰጠው ያለኝ ምስክርነት አለ ። ይህም በቁጥር አራት ላይ «ትርጉሙ መልእክቱ በልሳን ከመሰጠቱ በፊት ሊሰጥ ይችላል» ላልኩት በቂ ማስረጃ ሊሆን ይችላል ። አንድ ጊዜ የዩኒቨርሲቲ ክርስቲያን ተማሪዎች በኅብረት ባደረጉት ኮንፍራንስ ላይ እንድናገር ጠይቀውኝ በስብሰባቸው ላይ ተገኘሁ ። የሰጡኝ አርእስት ቀደም ብዬ በሌላ ሥፍራ የተናገርኩበት ስለ ነበር ብዙም አልተዘጋጀሁበትም ። በምስብክበት ጊዜ ስብከቱ እነርሱ እንደተጠበቁት እኔም እንዳሰብኩት አልሆነም ። መልእክቴን ለመጨረስ ስቃረብ ይህ በጣም ተሰማኝ ። መልእክቱን ጨርሼ የመዝጊያ ጸሎት ሳደርግ የእግዚአብሔር መንፈስ ወደእ መጣ ። በዚያው ጊዜ አንድ መልእክት ተሰጠኝ ። ምንም ጊዜ ቢሆን እንደማደርገው በጸጥታ የመልእክቱን ቃል በመመርመር ላይ እንዳለሁ ከጉባዔው መካከል አንዱ በልሳን መልእክት አመጣ ። በዚህ ጊዜ ሳልጠራጠር ቀደም ብዬ እግዚአብሔር የሰጠኝን ቃል ተናገርኩ ። ከዚያም ትርጉሙ ቀጠለ ። እግዚአብሔርም ከጠበቅነው በላይ የሆነ በረከት ሰጠን ፤ በእውነት እጅግ ደስ የሚያሰኝ ጊዜ ነበር ። የመተርጐም ስጦታ በእንደዚህ ያለ ጊዜ ለሰዎች የሚያስፈልገውን መልእክትና በረከት እንዲያገኙ ያደርጋል ።

በልሳናት ስለመናገርና መተርጐም ስጦታ በ፩ኛ ቆሮንቶስ ፲፬ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ድንጋጌ አውጥቷል ። መልእክቱ እንዴት እንደሚመጣ ከተነጋገርን ስለሚቀርብበትም ሁኔታ መነጋገር ግድ ይኖርብናል ። ተርበን ምግብ ለመብላት ተቀምጠን ሳለን በጥሩ ሁኔታ ባያቀርቡልን ለመብላታችን የጓጓነውን ያህል አንበላም ። እንደዚሁም መልእክቱ ሰዎችን የሚያንጽና የሚገነባ ሆኖ ሳለ በጥሩ ሁኔታ ካላቀረብነው ሰዎች ከመጠቀም ይልቅ ይሰናከላሉ ። ብዙውን ጊዜ ስጦታው ኖሮን ሳለ ጥሩ አቀራረብ ስለሌለን ሰዎች እንዲተቹ ይገደዳሉ ። ወደተነሳንበት ዋና ሀሳብ እንምጣና ሐዋርያው ጳውሎስ ፩ ቆሮ. ፲፬ ፣ ፳፯ በልሳን ስለ መናገርና ስለ መተርጐም ስጦታ አቀራረብ በሚገባ ገልጿል ። «በልሳን የሚናገር ቢኖር ሁለት ወይም ሦስት ሆነው በተራቸው ይናገሩ አንድም ይተርጉም» ስጦታው በዚህ ዓይነት ሁኔታ በቤተ ክርስቲያን ከተገለጸ ሁከት አይኖርም ። መንፈስ ቅዱስ ታላቅ ኃይል ነው ። ይህን ኃይል ለመልካም ልንጠቀምበት እንችላለን ። ይህን ካላወቅን ግን ብዙ እናጠፋና ራሳችንንም ችግር ውስጥ እንጥላለን ።

በዚህ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ አካባቢ ብዛት ያላቸው ወጣቶች ናቸው ። እንደ ዕድሜያቸውም በዚያው መጠን በክርስትና ሕይወታቸውም ወጣት ናቸው ።

እነዚህ ወጣቶች በጌታ ፍቅር ተይዘው በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው ከማየት የበለጠ ነገር የለም ። ቢሆንም እጅግ ስለሚሮጡና ስለሚቸኩሉ ብዙ ያጠፋሉ ። እዚህ ላይ በብዙ ልምምድ ውስጥ ያለፉ መሪዎች ትምህርት ከመስጠት መቆጠብ የለባቸውም ። በሌላ አንጻር በዕድሜ የበሰሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሊረዱት የሚገባ በቤተ ክርስቲያናቸው እንዲህ ያለ ልምምድ ያላቸው ወጣቶች ቢኖሩ ልዩነት ከመፍጠር ስህተቱ ከስጦታው ሳይሆን ከሰዎቹ መሆኑን አውቀው በትዕግሥትና በፍቅር መያዝ ያስፈልጋል ። ስጦታው ፍጹም ነው ተጠቃሚዎቹ ግን ፍጹማን አይደሉም ።

## የትንቢት ስጦታ ፤

ይህ ስጦታ ለቤተ ክርስቲያን እጅግ አስፈላጊና ጠቃሚ ነው፤ሐዋርያው ጳውሎስ በ፩ ቆሮንቶስ አሥራ አራተኛው ምዕራፍ ላይ ከየትኛውም ስጦታ ይልቅ ስለ ትንቢት ስጦታ ይናገራል ። «ፍቅርን ተከታተሉ፥መንፈሳዊ ስጦታንም ይልቁንም ትንቢት መናገርን በብርቱ ፈልጉ» «መንፈሳዊ ስጦታን በብርቱ የምትፈልጉ ከሆናችሁ ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ እንዲበዛላችሁ ፈልጉ...... ስለዚህ ወንድሞች ሆይ ትንቢት ለመናገር በብርቱ ፈልጉ።» ሐዋርያው እንደዚህ በመሳሰሉ ጥቅሶች ክርስቲያኖች ስጦታን የሚፈልጉ ከሆነ ስለ ትንቢት ስጦታ እንዲጸልዩ ያሳስባቸዋል ። ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያን እንዲታነጽበት ነው ።

ስለ ስጦታው አስፈላጊነት ከተነጋገርን ትንቢት ምንድን ነው? በሚል ሃሳብ ተነስተን ስጦታውን እንግለጸው ። ትንቢት እግዚአብሔር ስለ ራሱ ምስክር የሚሰጥበትና የሚገልጥበት መንገድ ነው ። ይህም በመሆኑ በብሉይ ሆነ በአዲስ የእግዚአብሔር መንፈስ በሰዎች ላይ ሲወርድ ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር በመዛመድ በሰዎች ሕይወት ውስጥ ተገልጧል ዘኍል. ፲፩ ፥ ፳፮ ፤ ሳሙ. ቀዳማዊ ፲ ፥ ፲ ፤ ሐዋ. ፲፱ ፥ ፮ ፤ በዮሐንስ ራዕይ «የኢየሱስ ምስክር የትንቢት መንፈስ ነው» የሚል የምናገኘው ለዚህ ነው ራዕይ ፲፱ ፥ ፲ ስለዚህ ትንቢት እግዚአብሔር ራሱን ከሚገልጥበት መንገድ አንዱ ነው ።

ትንቢት ምንድን ነው? ብለን ስንጠይቅ ሐዋርያው ጴጥሮስ «ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ» በማለት ትርጉሙን ይሰጠናል ። ይህ የትንቢት መሠረታዊ ትርጉም ነው ። ነገር ግን ይህን ትርጉም በሁለት አንጻር ልንመለከተው ይገባል ። ምክንያቱም በእግዚአብሔር ቃል ላይ የሰፈሩት ትንቢቶችና ዛሬ የሚነገሩት ልዩነት አላቸው ።

፩. በእግዚአብሔር ቃል ላይ የሰፈሩት ትንቢቶች ልንመረምር ልንፈትን አንችልም ። ምክንያቱም ተፈትኖ ያለፈ የነጠረ ቃል በመሆኑ ነው ።

፪. እያንዳንዱ ምዕመን በእግዚአብሔር ቃል በተሰጠው መብት መሠረት ዛሬ የሚነገሩትን ትንቢቶች መመርምር ፥ መፈተን ይችላል ። ቢሆንም ዛሬም የሚነገሩት ትንቢቶች በእግዚአብሔር ቃል ተፈትነው ካለፉ በኋላ የሚሰጣቸው ክብደት



በጴጥሮስ መልእክት ላይ እንደተገለጠው ነው ። አንዳንዶች «ትንቢት» የሚለውን ቃል «ሰባኪ» በሚል ይተረጉሙታል ፤ ፍጹም ስህተት ነው ። ስብከት አዘጋጅተን አጥንተን የምናቀርበው ነው ። ትንቢት ግን በዚያኑ ደቂቃ መንፈስ ቅዱስ ስጦታው ላለው ሰው የሚሰጠው ቃል ነው ። ሃሳቡ በተናጋሪው አእምሮ የሌለና ራሱም የሚገረምበትና እግዚአብሔርን የሚያመሰግንበት ሊሆን ይችላል ። ስለዚህ በብሉይ ሆነ በአዲስ አዘጋጅቶ የተነበየ የለምና ይህ ትርጉም ውድቅ ነው ።

ስለ ትንቢት ስጦታ ከተነጋገርን ሌላው ሳናነሳ የምናልፈው የሚሰጠውን ጥቅም ነው ። መቼም ትንቢት ሲባል ወደ አእምሮአችን የሚመጣው የወደፊቱን መግለጽ የሚል ሃሳብ ነው ። በብሉይ ኪዳን የሚሰጠው ትርጉም ይህን የመሰለ ቢሆንም ወደ አዲስ ኪዳን ስንመለስ ሰፋ ያለ ትርጉምና አገልግሎት እንዳለው እናያለን ። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚህ ሲናገር «ትንቢት የሚናገር ግን ለማነጽና ለመምከር ፥ ለማጽናናት ፥ ለሰው ይናገራል» ይላል ። ልሳን አማኙ ለእግዚአብሔር እንዲናገር የሚያስችለው ሲሆን ትንቢት ግን እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን ከሚናገርበት መሣሪያዎች አንዱ ነው ።

ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ሐዋርያው ጳውሎስ በአንደኛ ቆሮንቶስ ላይ ስለ ትንቢት ስጦታና ጥቅም መላልሶ ገልጧል ፤ በአዲስ ኪዳን ጥቅሙን በሥራ የሚያሳዩ ማስረጃዎች አሉ ። አንድ ጊዜ በኢየሩሳሌም የነበሩት ነቢያት ወደ አንጾኪያ በወረዱ ጊዜ ከመካከላቸው አጋቦስ የሚባል ነቢይ ተነስቶ ታላቅ ራብ እንደሚሆን ተነበየ ። በትንቢቱም መሠረት ደቀ መዛሙርት መዋጮ አደረጉ ሐዋ፥ ፲፩ ፥ ፳፯—፳፰ ሳኦል በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ከወንድሞች ጋር ሲጸልይ ጌታ በትንቢት ጥሪውን አረጋገጠለት ፤ ሐዋ. ፲፫ ፥ ፩ ፤ ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይወጣ ትንቢት ተነገረው ሐዋ. ፳፩ ፥ ፬ ፥ ፲፩ ፤ ጢሞቲዎስ በትንቢት ስጦታ አማካኝነት ስለ አገልግሎቱ ጌታ አረጋገጠለት ። (ጢሞ. ፬ ፥ ፲፬) ከእግዚአብሔር ቃል ከዚህም የበለጠ ማስረጃ ለመስጠት ይቻላል ። ነገር ግን መለስ ብለን ዛሬ ይህ ስጦታ የሰጠውን ጥቅም ለምስክር ያህል ባቀርብ ደስ ይለኛል ።

ከዛሬ አሥር ዓመት በፊት በቤተ ክርስቲያን በአንድ የጸሎት ፕሮግራም ላይ ለእግዚአብሔር ልሰጠው ስላለኝ አገልግሎት ስጸልይ አንድ ትንቢት ተነገረ ። ትንቢቱም የክርስቲያኖችን ድካምና ለአገልግሎት አለመዘጋጀት እግዚአብሔር ሊሠራ እንደሚፈልግ ፥ ሰው እንዳጣ ፡ በዚያ ፈንታ ሐሜት ፥ ጥላቻ በቤተ ክርስቲያን እንዳለ የሚገልጽ ነበር ። ይህን ትንቢት በሰማሁ ጊዜ የተሰማኝ ስሜት እጅግ ታላቅ ነበር ። መጽሐፍ እንደሚለው አጥንትና ጅማትን እንደሚለይ ነበር ። መዶሻ ድንጋይ እንደሚያደቅ አደቀቀኝ ። በሕይወቴ ያለውን ጉድለት አሳየኝ ። ስብሰባው አልቆ ወደቤቴ ከሄድኩበት ጊዜ አንስቶ ለአገልግሎት እስከወጣሁበት ጊዜ ድረስ ያ ትንቢት ለእግዚአብሔር ሥራ እንድዘጋጅ አድርጎኛል ። ይህ ብቻ ሳይሆን ስለ ጥሪዬ በምመሰክርበት ጊዜ ሁሉ ከምስክርነቴ ለይቼው አላውቅም ።

ዛሬም የትንቢት ስጦታ በቤተ ክርስቲያን መታነጽን ፥ መገንባትን ይሰጣል ። እንደዚሁ ተመሳሳይ የሆኑ ብዙ ምስክሮችን ማቅረብ ይቻላል ፤ ነገር ግን ስለትን

ቢት ስጦታ ከተነጋገርን እንዴት ትንቢት መናገር እንደሚገባን ጉባዔው የተነገረውን ትንቢት እንዴት መለየት እንደሚችል እንነጋገር ።

## ሀ/ እንዴት ትንቢት መናገር ይገባናል?

ትልቅ ትምህርት የሚያስፈልገው በዚህ ዐ ብይ ሃሳብ ላይ ነው ። ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው ላይ «በእያንዳንዳችሁ ትንቢት ልትናገሩ ትችላላችሁ» ብሏል ። ይህም ማለት ስጦታው በአንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለብዙ ሰዎች ሊሰጥ ይችላል ማለት ነው ፤ እንግዲህ በአንድ ጉባዔ ውስጥ ብዙ ስጦታው ያላቸው ሰዎች ኖረው በዚያው መጠን ትንቢቱ እንደ እግዚአብሔር ቃል ካልቀረበ ብዙ ትርምስምስ በጉባዔው ይፈጠራል ። ቀደም አድርጌ እንደገለጽኩት ስጦታዎች ፍጹም ሆነው ሳለ ከእኛ ከአቅራቢዎቹ ስህተት በመኖሩና የአቀራረብ ጥበብ ስለሚጐለን ሰዎች ስለ ትንቢት ያላቸውን አስተሳሰብ ዝቅተኛ እንዲሆን እናደርጋለን ።

ወደዚህ ሥፍራ ደርሼ ስጽፍ ጌታን የማመሰግነው የራሴን ልምምድ ለሰዎች ለማካፈል ዕድል በማግኘቴ ነው ። በሕይወቴ እግዚአብሔር በጸጋው ካስቀመጣቸው ስጦታዎች አንዱ የትንቢት ስጦታ በመሆኑ ከአጠፋሁትም ሆነ ካስተካከልኩት በመግለጽ ለአንባቢዎቼ እንደ ምሳሌ ባቀርብ ብዙ ትምህርት ያገኛሉ ብዬ እላለሁ ። በ፲፱፻፺፱ ዓ. ም. በግንቦት ወር እግዚአብሔር ይህን ስጦታ በሕይወቴ ያስቀመጠበት ሰዓቱና ቦታው አሁንም ትዝ ይለኛል ። እጅግ ደስ የሚያሰኝ በረከት ነበር ። ነገር ግን ከዚያ በኋላ ባደረኩት ስህተት ብዙ አጠፋሁ ። እግዚአብሔር በዚህ ሁሉ ጊዜ ባለማወቅ እንደማደርገው ያውቅ ነበርና ምህረቱን ከእኔ አላሸሸም ። ብዙ ማጥፋቴን በተረዳሁ ጊዜ ከእግዚአብሔርና ከቃሉ ለመማር ወስኜ ለሁለት ዓመት ስጦታውን ለመጠቀም አልፈለኩም ። ይህም በሕይወቴ እጅግ ረድቶኛል ። በእነዚያ ዓመታት ውስጥ ነው ፣ በመጽሐፍ ቅዱስና የእግዚአብሔር ሰዎች በጻፉት መጻሕፍቶች እንዲሁም በጸሎት እግዚአብሔር አስተካከሎኝ፤ የስሜትን ሥራ ከመንፈስ ለይቼ ለማወቅ የቻልኩት ፣ በእነዚያ ሁለት ዓመታት ውስጥ ነው የእግዚአብሔር ቃል ወደኔ ሲመጣ ከመናገር ይልቅ ለራሴ በመያዝ እጠብቀው ነበር እንጂ አልቸኩልም ነበር ። ከሁለት ዓመት በኋላ ከአንድ ወንድም ጋር ስንጸልይ በማያጠራጥር ሁኔታ እግዚአብሔር የሰጠኝን እንድናገር ተናገረኝ ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስከዚህ ጊዜ እግዚአብሔር በሰጠኝ ጸጋ ቤተ ክርስቲያንን አገለግላለሁ ።

ስለዚህ ካገኘሁት ልምምድና ከእግዚአብሔር ቃል እንደተረዳሁት የትንቢት ስጦታ ያላቸው ወንድሞችና እህቶች መረዳት ያለባቸውን አምስት ነጥቦች አቀርባለሁ ።

፩. <u>የእግዚአብሔር ቃል ከሁሉ በላይ መሆኑን መረዳት</u> ፣ የትኛውም ስጦታ ያለው ክርስቲያን ሊገነዘብ የሚገባው ዋናና ቀዳሚ ነገር የእግዚአብሔር ቃል የስጦታዎች ሁሉ መፈተኛ ሚዛን መሆኑን ነው ። ይህም ሲሆን የክርስቲያኑ ሕይወት መሠረት የሚያገኘው በመገለጥ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቃል ነው ። ሐዋርያው ጴጥሮስ እንደሚናገረው ፣ «ከእርሱም ይልቅ እጅግ የጸና የትንቢት ቃል አለን»



ይላል ፪ኛ ጴጥ. ፩ ፣ ፲፱ ስለዚህ ስጦታ ያለው ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ቃል የማጥናት ኃላፊነት አለበት ።

በጥንት የነበሩ ነቢያት ዋና ሥራቸው በእሥራኤል አደባባዮች ቆመው መተንበይ ብቻ ሳይሆን ብዙ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት መጻሕፍትን በመመርመር ነበር ። ስለዚህም ሐዋርያው ጴጥሮስ ሲናገር «ትንቢት የተናገሩ ነቢያት ስለዚህ መዳን ተግተው እየፈለጉ መረመሩት» ይላል ፩ ጴጥ. ፩ ፣ ፲ ፤ ስጦታ ያለው ክርስቲያን መሠረት የሚመረመረው የተናገረውን ትንቢት ወይም የሰጠውን መገለጥ ሌሎች ለመለየት ወደ እግዚአብሔር ቃል ሄደው ሲያመዛዝኑ ነው ። አንዳንዶች ትንቢታቸው ሆነ የሰጡትን መገለጥ ሌሎች በማኅበር ሆነ በግል ሲፈትኑት አይደሰቱም ። ይህን ከመጠራጠር ፣ ከአለማመን ይቆጥሩታል ። የሚደሰቱት ትንቢታቸውን ሰዎች በሃሌ ሉያና በአሜን ብቻ ሲቀበሉት ነው ፤ ነገር ግን እያንዳንዱ ክርስቲያን ትንቢቶችን ሆነ መገለጦችን የመመርመር ፣ የመፈተን መብት በእግዚአብሔር ቃል ተሰጥቶታል ። «መንፈስን አታጥፉ ፣ ትንቢትን አትናቁ ፣ ሁሉን ፈትኑ ፣ መልካሙን ያዙ» (፩ ተሰሎ. ፭ ፣ ፲፱—፳፩) በተጨማሪም ፩ ቆሮ. ፲፬ ፣ ፳፱ ፤ ፩ ዮሐ. ፬ ፣ ፩ ፤ የእግዚአብሔር ቃል ከመገለጥ ፣ ከትንቢት ሁሉ በላይ ነው ።

## ፪. የትንቢት መገለጥ እንደተገኘ ወዲያው ከመተንበይ በእግዚአብሔር ፊት መቆየት

ብዙዎች የመጀመሪያውን ሁለትና ሦስት ቃላት እንደተቀበሉ ካለምንም መቆየት ወዲያው ተነስተው ይተነብያሉ ። እንዲህ ያሉ ሰዎች እግዚአብሔር ተናግሮአቸው እስኪጨርስ ትዕግሥት ስለሌላቸው ከእግዚአብሔር በሰሙት አንድ ዓረፍት ነገር ቢጀምሩ ከእነርሱ በሆነ አምስት ዓረፍተ ነገር ይጨርሳሉ።በእግዚአብሔር ፊት በጸጥታ ለተወሰኑ ደቂቃዎች መቆየት የሚያስፈልግበት ምክንያቶች አሉ ። ፩ኛ/ እግዚአብሔር ለጉባዔው እንድናስተላልፍ የሚሰጠን ቃል አድምጠን ለመጨረስ ፣ ፪ኛ/ እግዚአብሔር የሰጠንን ብቻ ለመናገር ከሥጋችን እንዳንጨምር ራሳችንን በእግዚአብሔር እጅ አሳልፈን ለመስጠት ፣ ፫ኛ/ መልእክቱን የምናስተላልፍበት ትክክለኛ ጊዜና ሁኔታ ለመፈለግ ናቸው ።

## ፫. <u>እግዚአብሔር የሰጠንን ብቻ መናገር</u> ፤

አንዳንድ ሰዎች ከተነበዩ ለረጅም ጊዜ መተንበይ እንዳለባቸው ያስባሉ ። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ቃል እንደምናነበው ነብያት እግዚአብሔር ከሰጣቸው አላሳነሱም አልጨመሩም ። ዛሬ የእግዚአብሔርን ድምጽ የምንሰማው በረጅም ትንቢት ውስጥ ብቻ አይደለም ። ነገር ግን እግዚአብሔር በጥቂቱ በመናገር መጠገንን ፣ መፈወስን ይሰጠናል ።

ከአምስት ዓመት በፊት ጥቂት ወንድሞች ሆነን በአንድ የመናፈሻ ሥፍራ ስንጸልይ አንድ አጭር ትንቢት ተነገረ ፤ ቃሉም የሚለው «ለብዙ ሰዎች በረከት አደርጋችኋለሁ» ነበር ። አንድ ዓረፍተ ነገር ነው ። ነገር ግን ከእግዚአብሔር የመጣ መልእክት ነበር ። በዚያን ጊዜ ቤተ ክርስቲያን በስደት ላይ ነበረችና የጌታን ወን

ጌል የት ቆመን ሰብከን ለብዙዎች በረከት እንሆናለን? የሚል ጥያቄ በሁላችን አእ ምሮ ሳይመጣ አልቀረም ፤ ነገር ግን በማንኛችንም ዘንድ ከመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ወንድሞች ጋር በመሥራት ለብዙዎች በረከት እንሆናለን ብለን አልገ መትንም ። ዛሬ ከአምስት ዓመት በኋላ የዚህች ቤተ ክርስቲያን መጋቢ ሆኜ ራሴን ሳገኘው በእግዚአብሔር ሥራ እደነቃለሁ ። እግዚአብሔር በዚህም በዚያም መንገድ ይሠራል ሰው ግን አያስተውልም ።

ሰዎች ለትንቢታቸው መርዘም ሁለት ችግሮች አሉ ። ፩ኛ/ ትንቢት የሚናገ ረው ሰው የተሰጠው ቃል አጭር ሆኖ ሳለ ያንኑ ቃል በመደጋገም ይናገራል ። ምና ልባት ሃሳቡን በሌላ ቃላት ቢናገረውም የሚደግመው ያንኑ ሃሳብ ነው ። የእግዚ አብሔር መንፈስ እንድንደግመው ካልተናገረን በስተቀር ሃሳቡን ሆነ ቃሉን መደጋገም አይጠቅምም ። በዚህ ላይ ሳይጠቀስ የማይታለፈው ወይም ይህ ስጦታ ያላቸው ሊገነዘቡ የሚገባው ቃሉ በታላቅ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ወደ ክርስቲያኑ ሲመጣ በነፍስና በአጥንት ውስጥ እንደ ሚነድ እሳት መሆኑን ነው ። ስጦታው ያለው ክርስቲያን የትንቢቱ ቃል በውስጡ በታላቅ ኃይል ሲያስተጋባ የትንቢቱን ቃል ይናገራል ። ከተናገረም በኋላ ያንኑ ድምጽ በውስጡ ሊሰማ ይችላል ። ይህ የሚሆንበት የትንቢቱ ቃል በመንፈስ ኃይል የተሞላ ስለሆነ ነው እንጂ ያንኑ ቃል ተነስቶ መናገር ስላለበት አይደለም ። ብዙውን ጊዜ ይህ የሚሆነው ክርስቲያኑ ስጦ ታውን በተቀበለ ሰሞን ነው ። ፪ኛ/ አንዳንድ ሰዎች በተነበዩ ቁጥር ሳይናገሩት የማ ያልፉት ዓረፍተ ነገር አላቸው ። ዛሬ በሀገራችን ካሉት ሰባኪዎች አንዱ ድሮ ትን ቢት በሚናገርበት ጊዜ ሳልናገረው የማላልፈው አንድ ጥቅስ ነበር አለ ። እርሱም በትንቢተ ሚልክያስ ላይ ያለው «እንደ ምድጃ እሳት የሚነድ ቀን ይመጣል» የሚለው ነው ። እንግዲህ ሌላውም ከመጽሐፍ ቅዱስ ሆነ ከራሱ ሳይጠቅሰው የማያልፈው ዓረፍተ ነገር ካለ እግዚአብሔር የሰጠው አጭር መልእክት ሆኖ ሳለ ተናጋሪው ስለ ሚጨምርበት ይረዝማል ። ስለዚህ የትንቢት ስጦታ ያላቸው ክርስ ቲያን እህቶችና ወንድሞች እግዚአብሔር የሰጣቸውን ብቻ መናገር ይኖርባቸዋል ። ሚክያስ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ይሆነናል ። «ሕያው እግዚአብሔርን! አምላኬ የሚለውን እርሱን እናገራለሁ» ዜና መዋልዕ ካልዕ ፲፰ ፣ ፲፫ ፤

## ፬. ትንቢት በምናቀርብበት ጊዜ ሁከት አለመፍጠር ፤

ሁልጊዜ ሁከት የሚፈጥሩት አድማጮች ምዕመን ብቻ አይደሉም ። አንዳን ዴም ተናጋሪው ችግር የሚሆንበት ጊዜ አለ ። ይህም የሚሆነው ሕዝቡ ለማዳመጥ በፍጹም ጸጥታ ሳለ ተናጋሪው አስፈላጊ ባልሆነ በታላቅ ድምጽ መተንበይ ይጀ ምራል ። በእውነት ለሚያደምጥ ጩኸት እንጂ ትንቢት አይመስልም ። ተናጋሪውም እጅግ ስለሚጮኸ በዚያው ድምጽ ሊቀጥል አይችልም ። ማሃል ላይ ሲደርስ ጉሮሮው ይዘጋል ወይም ትን ይለዋል ወይ ጉሮሮው ስለታፈነ ሁሉን ረስቶ መሳል ይጀም ራል ። ይህ ሁሉ የታየ ነገር ነው ። እንግዲህ እዚህ ላይ ማሰብ የሚገባን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ስብሰባው የመጡ ሰዎች መኖራቸውን ነው ። ከትንቢቱ ሊጠቀሙና



ሊነኩ ሲችሉ ባዩት ነገር ስቀውና አፌዘው ሁለተኛ ወደ ጸሎት ቤት ለመሄድ መቼም ቢሆን ፈቃደኛ አይሆኑም ። ለዛውም ደግሞ «መንፈስ ቅዱስን የሰደበ አይ ሠረይለትም» የሚለውን ጥቅስ እንጠቅስባቸዋለን ። መንፈስ ቅዱስን ያሰደብን እኛ ስንሆን እርግማቱን ከእኛው ብንጀምር ይሻላል ። በአሥር ሰዎች መካከል ትንቢት የሚናገር በአንድ ሺህ ሕዝብ ፊት እንደሚናገር ያህል ድምጹን ከፍ ማድረግ አይኖ ርበትም ። ምናልባት ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት መልእክት ቢሰጠን ወደፊት በመሄድ ከመሪው ፈቃድ በመጠየቅ በድምጽ ማጉያው መልእክቱን ለማስተላለፍ ይችላል ።

በዚሁ አንጻር መታየት ያለበት በሰውነት የሚደረገው እንቅስቃሴ አስፈላጊ አለመሆኑን ነው ። አንዳንዶች ሲተነብዩ የተቀመጡበትን ወንበር ካልደበደቡ እንገታቸውን ካላሽከረከሩ መተንበይ የሚቻል አይመስላቸውም ። እኔ እንዳለፍኩ በት ልምምድ ከሆነ አንገት ማሽከርከሩና ወንበር መደብደቡ ትንቢቱን ሞቅ የሚ ያደርግ ይመስላል ። የዛሬ አሥራ አንድ ዓመት ስወዘውዘው የነበረ ወንበር እስከ አሁን ተጣሞ ለምስክር ይገኛል ። እንደ እውነቱ እንዲህ ያለው ነገር ሁከት ከመፍ ጠሩ በስተቀር ጥቅም አይሰጥም ። እግዚአብሔር የሰላም አምላክ እንጂ የሁከት አምላክ አይደለም ።

## ፭. ስጦታውን ለግል ጉዳይ አለመጠቀም ፤

እልፎ አልፎ የሚታየው ስህተት ስጦታውን ለግል ጉዳይ መጠቀሚያ መሆኑ ነው ። ስለ ትዳር ፣ ስለ ሥራ ፣ ስለ ገንዘብ ጉዳይ የሚነገሩ ትንቢቶች አደገኛ ናቸው ። አንዳንድ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ፈቃድ በአንዳንድ ግላዊ ጉዳዮች ላይ ለማወቅ ስጦታው ካለው ክርስቲያን ጋር ይጸልያሉ ። ዓላማው በትንቢት ስጦታ አማካኝነት ከእግዚአብሔር ለመስማት ነው ። ፍጹም ስህተት ነው ። ትንቢት በልባችን የተገለጸውን ያረጋግጥልናል እንጂ ለመመሪያ አንጠቀምበትም ። ይህም በእግዚአብሔር ቃል ግልጽ ሆኖ የሚታይ ነው ፤ ለማስረጃ ያህል በሐዋ. ፲፫ ፣ ፪ ያለውን እንመልከት ፣ «በርናባስንና ሳኦልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ» የሚል ትንቢት ተነገረ ። ይህ ትንቢት በርናባስን ሆነ ሳኦልን የሚያስደነግጥ አልነበረም ። ምክንያቱም ቀደም ብሎ ጥሪውን ሰምተው ነበር ። ትንቢቱ ጥሪውን አረጋገጠላ ቸው ።

ነገር ግን በትንቢት ስጦታ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ የሚፈልግና ለመ መራት የሚወድ ቢኖር ራሱን ከፈተና ላይ ከመጣሉም ሌላ ፈተናው እግዚአብሔር በኃላፊነት የማይጠየቅበት ነው ።

## ለ/ «ሁሉን ፈትኑ» ትንቢትን ማድመጥና መመርመር

ባለፉት ገጾች ስለ ትንቢት መናገር አንዳንድ ነጥቦችን በመጥቀስ አብራርቻ ለሁ ። በዚያው አንጻር እንዴት ትንቢት መስማት እንዳለብንና ትንቢትን ስለመመ ርመር መነጋገር አስፈላጊ ነው ።

ከሁሉ አስቀድሜ ትንቢትን እንዴት ማድመጥ እንደሚገባን መነጋገር ይኖርብናል ። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሲገለጡ ሥርዓት የሚያፈርሱ ተናጋሪዎች ብቻ ሳይሆኑ አድማጭ ምዕመናኖችም ጭምር ናቸው ። ብዙ ጊዜ በመሪዎች እንደ ተገለጠው ትንቢት ሲነገር ሃሌ ሉያ በማለት የሚያስተጋባው የምእመን ድምጽ አስፈላጊ ካለመሆኑም በብዙ አቅጣጫ ችግር ይፈጥራል ። ፩ኛ/ ተናጋሪው አንድ ቃል ሲናገር ምዕመኑ በሃሌሉያና በአሜን የሚያስተጋባ ከሆነ ክርስቲያኑ ወደ እግዚአብሔር ከመመልከት ወደራሱ እየተመለከተ ቀስ በቀስ ከመንፈስ ቁጥጥር በመውጣት በስሜት በመሞላት ብዙ ነገር ከሥጋው ይጨምራል ። ፪ኛ/ ትንቢቱን ለማድመጥ የሚፈልጉ ክርስቲያኖች የተናጋሪው ድምጽ በሃሌሉያና ፥ በአሜን ፥ ስለሚዋጥ ለማድመጥም ሆነ ለመመርመር አይቻልም ። እንግዲህ ይህንና ሌሎች ችግሮችንም የሚፈጥር ከሆነ ምዕመን በፍጹም ሊያስተካክሉት የሚገባ ነገር ነው ። አንዳንዶች ገና ተናጋሪው ትንቢቱን ሲጀምር የጀመረውን ዓረፍተ ነገር ሳይጨርስ መጮህ ይጀምራሉ ። አንዳንዶች ስጦታው ያላቸው እንዲህ ዓይነቱ ሁከት ሲነሳ የተሰጣቸውን መልእክት ሳይጨርሱ ይቀመጣሉ ምክንያቱም በሚሆነው ሁከት መንፈሳቸው ስለሚረበሽ ነው ።

እጅግ አድርጌ የምፈራው ይህን ሁከት ሰይጣን እንዳይጠቀምበት ነው ። በአንዳንድ ሥፍራ እንደታየው ክርስቲያኖች ያልሆኑ ጌታን ያልተቀበሉ ፥ ነገር ግን በአጋንንት መንፈስ የተሞሉ ተነስተው እርግማንና ፍርድ የተሞላበት ትንቢት ሲናገሩ ተሰምተዋል ። በፍጹም ከኃላፊነቱ ለመሸሽ አንችልም ። የእግዚአብሔር ቃል ሁሉ ይታነጹ ዘንድ በአግባብና በሥርዓት ይሁን ይላል ። በአግባብና በሥርዓት የምናደርገው ነገር ሰዎችን ይማርካል ። በእውነት እግዚአብሔር በመካከላቸው ነው ብለው እግዚአብሔርን ያከብራሉ ። በአንዳንድ ትላልቅ ስብሰባ ላይ በመካፈላችን የማይደሰቱ ሰዎች አሉ ምክንያቱም ሁከት ፈጣሪዎች በመባል በመታወቃችን ነው ። እነዚህ ጴንጤዎች መጡብን ከመባል መጡልን መባሉ የተሻለ ነውና የእግዚአብሔርን የጸጋ ስጦታዎች በአግባብ በመጠቀም ሌሎች ወንድሞቻችንን ለዚህ በረከት እንማርካቸው ።

እንዴት ትንቢቶችን ማድመጥ እንደሚገባን ከተረዳን ትንቢቶች ከእግዚአብሔር እንደሆኑ ወይም እንዳልሆኑ እንዴት ማወቅ እንችላለን? የሚለውን ሃሳብ እንነጋገርበት ብዙ ክርስቲያኖች እንደሚመስላቸው መለየት የሚችሉ ወይ የሚገባቸው የመናፍስት መለየት ስጦታ ያላቸው ብቻ ናቸው ብለው ያስባሉ ። ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል ይህን አያስተምረንም ። ቃሉ የሚለው «ወዳጆች ሆይ ፥ መንፈስን ሁሉ አትመኑ ፥ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደ ሆነ መርምሩ» ፩ ዮሐ. ፬ ፥ ፩ ፤ የጌታ የሆኑ ሁሉ በጉባዔው የተቀመጡት ለመመርመር፥ ለመለየት ሥልጣን አላቸው ። ፩ ቆሮ. ፲፬ ፥ ፳፱ ፥ ፩ ተሰሎ. ፭ ፥ ፲፱ ስለዚህ እያንዳንዱ ክርስቲያን ትንቢቶች ሆኑ መገለጦች ወደርሱ ሲመጡ መመርመር ፥ መለየት አለበት ።

እንዴት ትንቢት መናገር ይገባናል የሚለውን ሃሳብ ከተነጋገርንበት በመጨረሻ ልንነጋገርበት የሚገባ ነጥብ እንዴት ትንቢትን መመርመር እንደሚገባን ነው ።



አስቀድሜ እንዳልኩት ትንቢትን መለየት የተሰጠው መናፍስት መለየት ላላቸው ብቻ ሳይሆን ለእያንዳንዱ ክርስቲያን ነው ። የእግዚአብሔር ቃል ከሁሉ በላይ ነው ። ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል የሚሰጠን የመፈተኛ ቁልፎች አሉ ። እነዚህንም በየተራ በመጥቀስ እንነጋገርባቸዋለን ።

፩/ <u>የሚለያይ ትንቢት ከእግዚአብሔር አይደለም ፤</u>

የእግዚአብሔር ቃል በየትም ሥፍራ የሰዎችን መለያየት የቤተ ክርስቲያንን መከፋፈል አይደግፍም ። ስለዚህ ከተነገረው ትንቢት የተነሳ መለያየት ፥ መከፋፈል የተፈጠረ እንደሁ ያን ትንቢት አንቀበለውም ። ጌታ ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ አሥራ ሰባት ከጸለየው ጸሎት የምናነበው አንድ ነገር ስለ ክርስቲያኖች አንድነትና ፍቅር የጸለየው ነው ። «አንተ አባት ሆይ! በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ ፥ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምንሃለሁ ። እኛም አንድ እንደሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ........» ዮሐ. ፲፯ ፥ ፳—፳፩ ፤ የሚያለያይ ትንቢት ልንመለከተውና ልናስተውለው የሚገባው በቤተ ክርስቲያን ደረጃ ብቻ ሳይሆን በግለሰብም ደረጃ ነው ። ባልና ሚስትን የሚያለያይ ፥ በሚፋቀሩ መካከል መለያየት እንዲሆን የሚነገር ትንቢት ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም ።

ምንም ጊዜ ቢሆን እግዚአብሔር አንድነትና ፍቅርን እንጂ ጥላቻ ፥ ጠብን መለያየትን የሚደግፍ አይደለም ።

፪/ <u>ፍርድ የተሞላበት ትንቢት ከእግዚአብሔር አይደለም ፤</u>

ትንቢት ለቤተክርስቲያን የተሰጠ ክርስቲያኖች የሚታነጹበት ስጦታ ነው ። ይህ ሆኖ ሳለ ትንቢት ክርስቲያኖችን የሚያወግዝና የፍርድ ቃል የተሞላበት ከሆነ ልንቀበለው አይገባም ። ጳውሎስ «በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም» ሲል ይናገራል ። ሮሜ. ፰ ፥ ፩ ፤ እግዚአብሔር በትንቢት ስጦታ አማካኝነት ቤተ ክርስቲያንን እንደሚገስጽ ፥ እንደሚመክርየተረጋገጠ ነው ። ይሁን እንጂ ትንቢቱ በግሳጼ ቢጀመር በማጽናናት መጨረስ ይኖርበታል ። እግዚአብሔር ሰብሮ የሚጠግን እንጂ ሰብሮ የሚተው አይደለም ። ለዚህም በትንቢተ ሆሴዕ ፮ ፥ ፩—፪ ያለውን መመልከት በቂ ነው ። «ኑ ወደ እግዚአብሔር እንመለስ እርሱ ሰብሮናልና እርሱም ይፈውሰናል ፥ እርሱ መትቶናል እርሱም ይጠግነናል ። ከሁለት ቀን በኋላ ያድነናል ፥ በሦስተኛውም ቀን ያስነሳናል ፥ በሕይወትም እንኖራለን» ይላል ። በተለይ ነብዩ ኤርምያስ ለአገልግሎት በተጠራበት ጊዜ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ቃል በጣም አስገራሚ ነው ። «እግዚአብሔርም እጁን ዘርግቶ አፌን ዳሰሰ ። እግዚአብሔርም እነሆ ቃሌን በአፍህ ውስጥ አኑሬአለሁ ። እነሆ ትነቅልና ታፈርስ ዘንድ ታጠፋና ትገለብጥ ዘንድ ፥ ትሠራና ትተክል ዘንድ በአሕዛብና በመንግሥታት ላይ ዛሬ አድርጌሃለሁ» ኤር. ፩ ፥ ፱—፲ ፤ ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው የኤርምያስ አገልግሎት የማፍረስ ፥ የመገልበጥ የመንቀል ነው ። ምንም እንኳን በግሳጼና በፍርድ የጀመረ ቢሆንም የሚደመድመው በመሥራትና በመትከል ነው ።

እንግዲህ በአጠቃላይ ስንመለከት እግዚአብሔር ልጆቹን ይገስጻል ። ይሁን እንጂ በዚያው መጠን ያጽናናል ይገነባል ። እንግዲህ ይህ ከሆነ በፍርድ ጀምሮ በፍርድ የሚጨርስን ትንቢት እንቀበልም ፤ እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል?

፫/ እግዚአብሔር የማይከበርበት ትንቢት ተቀባይነት የለውም ፤

የትንቢቱ ቃል ማንን ከፍ የሚያደርግ ነው ። ወይም ወደ ማን የሚያተኩር ነው? ምንም ጊዜ ትንቢትን በሰማን ጊዜ ልንጠይቀው የሚገባ ነው ። አንዳንድ ትንቢቶች ጌታን የሚያከብሩ ፥ ወደ ጌታ እንድንመለከት የሚያደርጉን ሳይሆኑ ተናጋሪውን ወይም ሌላ ሰው የሚያወድሱ ይሆናሉ ። ጌታ ኢየሱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር «እርሱ በመጣ ጊዜ ያከብረኛል» ብሏል ። ስጦታዎች ሁሉ የስጦታው ጌታ የሆነውን ኢየሱስን የሚያከብሩ መሆን አለባቸው ።

፬/ የትንቢቱ መልእክት የተጨበጠ መሆን አለበት ፥—

አንዳንድ ትንቢቶች የተጨበጠ መልእክት የላቸውም ፤ አይዟችሁ ፥ በርቱ ፥ ከሚል መልእክት አያልፍም ። እርግጥ ተናጋሪው በተቀደሰ አእምሮ ስለሚናገር የሚናገረው ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰኑ ጥቅሶችን ሊሆን ይችላል ። ቃሉ አይጐዳም ። በሌላ አንጻር ለጉባዔው ጥቅም አይሰጥም ። የሚያስፈልገን መጽናናት ሆነ ምክር ከእግዚአብሔር የመጣ እንደሚፈስ ዘይት የሆነ ወይም ሁለት አፍ እንዳለው ሰይፍ መሆን አለበት ።

፭/ ትንቢት ሁሉ ከእግዚአብሔር ቃል መስማማት አለበት ፥—

ይህ ከሁሉ የላቀውና የበለጠው ሚዛን ነው ። ጴጥሮስ ሲናገር «ከእርሱም ይልቅ የጸና የትንቢት ቃል አለን» ይላል ፪ ጴጥ፥ ፩ ፥ ፲፱ ፤ ትንቢት ሆነ መገለጥ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ተፈትኖ ማለፍ አለበት ። ይህ የጸና የትንቢት ቃል ማለት መጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ተፈትኖ ያለፈ ከወርቅና ከብር ይልቅ የነጠረና የጠራ ነው ።

እንግዲህ ከብዙ በጥቂቱ እነዚህ የመመዘኛ ቁልፎች እጅግ ጠቃሚዎችና ስጦታው ያላቸው ሰዎች ድካም የሚያተኩርበት ነው ።



## ምዕራፍ ፲፩ ፤

# የመገለጥ ስጦታዎች

እውቀት መናገር ፥ ጥበብ መናገር ፥ መናፍስት መለየት ፤

የእውቀት መናገርና የጥበብ መናገር ስጦታዎች የሚገናኙበት ብዙ አቅጣጫ ስላለ ሁለቱን ባንድነት ስንመለከታቸው መናፍስት መለየትን ስጦታ ብቻውን እንመለከተዋለን ።

የእውቀት መናገር ስጦታ ሰማያዊ መገለጥ ስለ አለፈው ስለ አሁኑ ፥ ስለ ወደ ፊቱ ፥ የሚገልጥ ነው ። ይህ በትምህርት የሚገኝ ወይም በሰው አእምሮ የሚደረስበት ሳይሆን በዚያ ወቅት መንፈስ ቅዱስ ስጦታው ለተሰጠው የሚገልጠው ነው ። ስጦታው ክርስቲያኑ እንዴት እንደሚጸልይ ሌሎችን እንዴት እንደሚረዳ ያሳየዋል ።

ጥበብን የመናገር ስጦታ በእውቀት መናገር ስጦታ አማካኝነት የተሰጠውን እንዴት ፥ መቼ እንደሚገልጸው የሚሰጥ ጥበብ ነው ። ብዙ ጊዜ ጥበብን መናገር ከእውቀት መናገር ጋር አብሮ ይሰጣል ። ይህም ማለት በእውቀት መናገር ስጦታ በኩል የተሰጠንን ይዘን መሮጥ ሳይሆን መቼ? እንዴት? እንደምንገልጸው መጠበቅ አለብን ፤ በዚያው ወቅት ጥበብን መናገር ይሰጠናል ።

እውቀት ፥ ጥበብ ፥ የሚሉት ቃላት በብዙ አቅጣጫ ሊተረጐሙ የሚችሉ በመሆናቸው ትክክለኛውን ትርጉም ለመስጠት እርግጠኛ መሆን አለብን ። ቃሉ የእውቀት ስጦታ የጥበብ ስጦታ አይደለም ነገር ግን ቃሉ የሚለው የእውቀት መናገር የጥበብ መናገር ስጦታ ነው ። «መናገር» የሚለው ቃል በትርጉሙ ላይ ታላቅ ለውጥ ያመጣል ። ምክንያቱም «መናገር» የሚለው ቃል ስጦታ ያለው መንፈስ በሰጠው ወቅት በመንፈስ ቅዱስ አንድ ዓይነት መገለጥ እንደሚያመጣ የሚገልጽ ነው ። እውቀት ወይም ጥበብ ብለን ስንናገር አራት ዓይነት እንዳሉ ለመግለጽ ይቻላል ።

፩. የሰው ጥበብ ወይም እውቀት ፥ ይህ በዓለም ያለው ጥበብና እውቀት ሲሆን ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ የሚሄድ ነው ። በዳንኤል መጽሐፍ ላይ በግልጽ እንደተነገረው «ብዙዎች ይመራመራሉ እውቀትም ይበዛል» ዳን ፲፪ ፥ ፬ ፤ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚህ ጥበብ ሲናገር «ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም ። በመንፈስም የሚመረመር ስለሆነ ሊያውቀው አይችልም ። ምድራዊ ጥበብ ወደ ሰማያዊ ጥበብ ሊያደርስን አይቻልም ። ምክንያቱም መንፈሳዊ እውቀት ማለት የጌታን አእምሮ መያዝ ነው ። «እኛ የክርስቶስ ልብ አለን» ስለዚህ

መንፈስ ቅዱስ እንዳልነበር ለየ ። መንፈሱም ከእርሷ እንዲወጣ በኢየሱስ ስም አዘዘው ፣ መንፈሱም በዚያው ሰዓት ለቀቃት ።

ርኩሳን መናፍስት ለማታለል የሚሞክሩት ኃይማኖታዊ የሆነ መልክ ይዘው በመምጣት ነው ። ጥቅስን በመጥቀስ መንፈሳዊ ቃላትን በመደርደር የእግዚአብሔር ሰዎችን ለማደናገር ይሞክራሉ ። ይህ ሊለይና ሊታወቅ የሚችለው በመናፍስት መለየት ስጦታ ብቻ ነው ። ዛሬም በተለይ መንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በሚሠራበት አካባቢ ሰይጣን ለማደናገርና በማስመሰል ሕይወታቸውን በተቆጣጠረ ሰዎች በመጠቀም ብዙ ነገር ለማድረግ ይሞክራል ።

የመናፍስት መለየት ስጦታ የክርስቲያኖችን ኅብረት ፣ አንድነት የሚጠብቅ ተቆጣጣሪ ነው ለማለት ይቻላል ። ክርስቲያኖች እግዚአብሔር መገለጥን ሲሰጣቸው ለመናገር ይፈራሉ ። በተለይ መናፍስት መለየት ስጦታ ያላቸው ክርስቲያኖች ስጦታውን በሥራ ላይ ለማዋል ይፈራሉ ። ምክንያቱም ፍርድ መፍረድ ስለሚመስላቸው ነው ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉን በእምነት እንድናደርገው ያስተምረናል ። «እንደ እምነታችን መጠን ትንቢት እንናገራለን» ብዙዎች እግዚአብሔር የሰጣቸውን ለመናገር እምነትና ድፍረት ስለሚያንሳቸው ስጦታውን በሥራ ላይ አያውሉትም ። ከላይ እንደገለጽኩት የመናፍስት መለየት ስጦታ የክርስቲያኖችን ኅብረት ይጠብቃል ። ምክንያቱም ሁልጊዜ ችግሩ የሚመጣው ከውጭ ብቻ ሳይሆን ከውስጥም በመሆኑ ነው ። ዛሬ እግዚአብሔር የተጠቀመበት ክርስቲያን ነገ የችግር ምክንያት ሊሆን ይችላል ።

የመናፍስት መለየትን ስጦታ ከብዙ አቅጣጫ ለማየት ይችላል ። ዋናው ግን ቤተ ክርስቲያንን ከልዩ መንፈስ ሥራ ለመጠበቅና ለመከላከል ነው ።



ምዕራፍ ፲፪ ፤

# የኃይል ስጦታዎች

ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት የኃይል ስጦታዎች የሚባሉት ፈውስ ፣ ተአምራት ፣ እምነት ናቸው ። ብዙ ክርስቲያኖች ስለዚህ ስጦታ ለመረዳትና ለማወቅ ይፈልጋሉ ። ምክንያቱም እጅግ አስፈላጊ ስጦታ በመሆኑ ፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በዚህ ምድር በተመላለሰበት ጊዜ ፈውስና ተአምራት ከአገልግሎቱ ተለይቶ አያውቅም ። ለሐዋርያትም የሰጣቸው አገልግሎት በድንቅና በተአምራት የተሟላ ነበር ። የኢየሱስ ተአምራዊ አገልግሎት ዛሬም አላቋረጠም ወደፊትም አያቋርጥም ለዚህም እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን ።

ሦስቱም ስጦታዎች የኢየሱስን ተአምራዊ ኃይል የሚገልጹ በመሆናቸው በአንድነት እንመለከታቸዋለን ። እግዚአብሔር ድንቅ በሆኑ ሁኔታዎችና መንገዶች ለሰዎች ፈውስን ይሰጣል ፤ ጌታ በእርሱ ለሚያምኑት በሰጠው ሥልጣን «እጆቻቸውን በድውያን ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ» ብሏል በጌታና በሐዋርያት ሕይወት እንደሚታየው ተአምራትና ፈውስ የተደረገው እጃቸውን በድውያን ላይ በመጫን በቃል በማዘዝ ነው ። ይህ እጅ መጫን መሠረታዊ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ስለሆነ ዛሬም ስጦታው ያላቸው እጅ በመጫን ለበሽተኛው ይጸልያሉ ። እጅ መጫን አስማት ወይም ስውር ምስጢር አይደለም ነገር ግን በእግዚአብሔር ቃል የተገለጸና በሚጸልየውና በሚጸለይለት ሰው መካከል የመገናኛ መስመር ነው ። ኢየሱስ ከእጅ መጫን ጋር ብዙ የተለያዩ መንገዶችን ተጠቅሟል ። እጆቹን በድውያን ላይ ጫነ ቃል ብቻ ተናገረ ፣ ዕውሩንም ጭቃ ቀብቶ ወደ ሴሎሂም ሄደ ፣ እንዲታጠብ አዘዘው ፤ ዛሬም ጌታ እነዚህን መንገዶች ሁሉ ይጠቀማል ።

እንግዲህ ስጦታው ያላቸው ክርስቲያኖች ታላቅ ኃላፊነት አለባቸው ። የመጀመሪያው ኃላፊነት የራሳቸውን ሕይወት መጠበቅ ነው ፤ አንዳንዶች እግዚአብሔር ሲጠቀምባቸው ክብርን ክብር ለሚገባው አይሰጡም ፤ ይህም ሕይወታቸው እየደከመና የጌታም ጸጋ እየራቃቸው ይሄዳል ። ሰዎችን ወደ ራሳችን እንዳንስብ በጣም መጠንቀቅ ይኖርብናል ። ሌላው ጉዳይ ስለጸለይንላቸው ሰዎች የምንሰጠው ምስክርነት ነው ። የጸለይንለት ሰው ካለበት በሽታ ነጻ ሳይሆን ስለ ጸለይንለት ብቻ እንደተፈወሰ አድርገን ብንመሰክር ጌታን አያስከብረውም ። የእኛ ኃላፊነት መጸለይ እንጂ መፈወስና ማዳን አይደለም ። ይህ ብቻ ሳይሆን ያልተፈወሱ ሰዎችን እንደ ተፈወሱ አድርገን መድኃኒታቸውን እንዲጥሉ ብናስገድዳቸው ችግር ላይ ልንጥላቸው እንችላለን ። ሰዎች በተፈወሱ ጊዜ በሰውነታቸው ያውቁታል ።

ይህ ስጦታ በሙላት የሠራባቸው ሰዎች በዓለም ላይ ጥቂት ከመሆናቸውም በላይ የተነሱትም አልፎ አልፎ ነው ። ዛሬ፤እግዚአብሔር፤እንዲህ ያለ ስጦታ ያላቸውን ሰዎች በማስነሳት አገራችንን እንዲጐበኝ መጸለይ ይኖርብናል፤። ቀደም ብዬ እንዳልኩት በፈውስ ፣ በተአምራት ፣ በእምነት ስጦታዎች መካከል መቀራረብ አለ ። ስለዚህ የተአምራት ማድረግ ስጦታ ያለው ክርስቲያን የእምነት ስጦታ ይኖረዋል ። በእርግጥ የእምነት ስጦታ ራሱን የቻለ ትርጉም አለው ፤ እግዚአብሔርን ለታላቅ ነገር ማመን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለታላቅ ሥራ በእምነት ማነሳሳት ይህ እምነት ማነሳሳት ይህ እምነት ስጦታ ነው ።

በዓለም ላይ ታላቅ አገልግሎት የሰጡትና ብዙ ፍሬ ያፈሩት የመገለጥና የኃይል ስጦታ ያላቸው ሰባኪዎች ናቸው ። እነዚህም ስጦታዎች ፈውስ ፣ የእውቀት መናገር ስጦታዎች ጐልተው የሚታዩት ናቸው ። ስለዚህ በአብያተ ክርስቲያናት መካከል የፈውስ ስጦታ እንዲሠራ ጌታን የሚጠይቁ ብዙዎች ናቸው ፤ በዚያው መጠን ስለዚህ ስጦታ ልንገነዘባቸው የሚገቡ አንዳንድ ነጥቦች አሉ ፤ እነርሱም እንደሚከተለው በአጭሩ እንመለከታቸዋለን ።

በመጀመሪያ ደረጃ መገንዘብ የሚገባን ማንኛቸውም ስጦታ የፈውስም ስጦታ ሥራ ላይ ሊውል የሚችለው እግዚአብሔር በሚፈቅድበት ጊዜ ብቻ ነው ። ስጦታው ያለው ክርስቲያን በፈለገበት ጊዜ በሽተኞች የሚፈውሱ ቢሆን በየሆስፒታሉ እየዞርን አልጋዎቹን ባዶ ባደረግን ነበር ። ከዚህ ጋር አያይዘን ማተኮር ያለብን ስጦታው ያላቸው ክርስቲያኖች ፕሮፌሽናል ፈዋሾች አለመሆናቸውን ነው ። ማንም ሌላውን በዚህ ዓይነት የሚመለከት ወይም ራሱን እንዲህ የሚቆጥር ቢኖር ተሳስቷል ። በመሠረቱ ያመኑት ሁሉ እጃቸውን በመጫን ለድውያን እንደሚጸልዩ እነርሱም እንደሚፈወሱ ተገልጧል ። ነገር ግን እግዚአብሔር በተለይ አንዳንድ ሰዎችን ለዚህ ጉዳይ ስለመረጣቸው በእነርሱ በኩል ድንቅን ያደርጋል ። ይህም ማለት እነዚህ ሰዎች ከእኛ የተለዩ ቅዱሳን ስለሆኑ ሳይሆን እግዚአብሔር ሊጠቀም ባቸው ስለፈለገ ብቻ ነው ።

ሌላው ነጥብ ተጸልዮላቸው ከተፈወሱ በኋላ በሽታው ስለሚመለስባቸው ሰዎች ነው ። ብዙ ጊዜ አንዳንድ ክርስቲያኖች የጸለዩላቸው ሰዎች ከተፈወሱ በኋላ በሽታው ሲመለስባቸው ሲያዩ ይበሳጫሉ ። አንድ ልንገነዘበው የሚገባ ነገር ቢኖር የእኛ ኃላፊነት መጸለይ እንጂ እንዲፈወሱ ወይም ፈውሳቸው እንዲጸና ማድረግ አይደለም ። ተአምራትና ፈውስ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው ። ይህም ሥራ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ መሆኑን አውቀን ለጌታ ስንተውለት እግዚአብሔር እርሱ እንደወደደ ይሠራል ።



# ማ ጠ ቃ ለ ያ ።

መንፈስ ቅዱስ እጅግ ሰፊና ትልቅ ርዕስ ነው ። በእነዚህ ባለፉት ገጾች ስለ መንፈስ ቅዱስ ዶክትሪንና ልምምድ ተናግሬ ጨርሻለሁ ማለት አይደለም ከዚህም በተሻለና ሰፋ ባለ ሁኔታ መጻፍ ይችላል ። ነገር ግን ጠቃሚና አስፈላጊ የሆኑትን ሀሳቦች አጠር አጠር አድርጌ አቅርቤአለሁ ።

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን በሚመለከት አስፈላጊ መስለው የታዩኝን ሃሳቦች ለስፍሬአቸዋለሁ ፤ ከእነዚህ የጸጋ ስጦታዎች ጋር በማያያዝ ስለ መንፈስ ፍሬዎች መረዳት ይኖርብናል ። የመንፈስ ፍሬ የማይታይበት የጸጋ ስጦታ ተቀባይነት አይኖረውም የመንፈስ ስጦታዎችና ፍሬዎች ሚዛናዊ በሆነ ሁኔታ በአንድ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ መታየት አለባቸው።ይህም ሲሆን ስለመንፈስ ፍሬ ብቻ ፣ሚናገሩ ማስተዋል ያለባቸው የጸጋ ስጦታዎች በሕይወታቸው መታየት እንዳለባቸው ነው ።

ቀደም ብዬ እንዳልኩት መንፈስ ቅዱስ ሰፊና ትልቅ ርዕስ በመሆኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ ስለ መንፈስ ቅዱስ ማንበብና መረዳት አለባቸው ። ከሁሉ በላይ ያለንበት ዘመን የመንፈስ ቅዱስ ዘመን በመሆኑ ብዙ ስለ መንፈስ ቅዱስ ማወቅ ይኖርብናል ። ይህንንም ጥማታችንን የሚያረኩ ብዙ መጽሐፍት ተጽፈዋል ።

*You may contact the author*
*at the following address:*

Daniel Makonnen
Ethiopian Community Evangelical Church
1906 H Street N.W.
Washington, D.C. 20006

Telephone: 202 / 898-1525